## ምዕራፍ ፲፱

## ዘዓርብ ስቅለት ዘንዋም ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር ሥላሴሁ ዘኢይትፌለጥ፡ወህላዌሁ ዘኢይትዌለጥ፡ በእድ እንተ ኢታስተርኢ ነፍሰ እጓለ እመሕያው ዘይመሥጥ፡ወአመ ትንሣኤ ሙታን ካዕበ ኀበ ማኅፈደ ሥጋሃ ዘይሠውጥ፡ሑረተ ፀሐይ ወወርኅ መንገለ መስዕ ዘይመይጥ፡ዘያንሕሎ ለዕፀ አውልዕ ወይጼንዖ ለብርዕ ቅጥቁጥ፡ ዘያበውኦ ለዘእንተ አፍኣ ወያወጽኦ ለዘእንተ ውስጥ፡ እስመ ውእቱ በዲበ ኲሉ ሥሉጥ፡ሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡

፪ ናንሥእ ርእሰነ እምንዋመ ሀኬት ከመ ንንግር ዘለፋሆሙ ለአርሲስ ወለመናፍቃን እለ ይብሉ በነፍስ ወሥጋ ወረደ ውስተ ሲኦል፡፡

፫ ኦ አብዳን ወኀጥኡአነ ምክር ወኀሊና በእንተዝኒ እበደ ስሕተትክሙ ይትፌቀድኑ ስምዐ መጻሕፍት፡፡ቅድሙኬ ንግሩነ ለሊክሙ ሞተኑ ትብልዎ ለወልደ እግዚአብሔር ወሚመ ኢሞተ፡፡ወእመሰ ትብልዎ ሞተ ዘከመ እፎ ትብሉ ወረደ ውስተ ሲኦል በነፍስ ወሥጋ፡፡ እለሰ ወረዱ ውስተ ሲኦል በነፍስ ወሥጋ ሕያዋኒሆሙሰ ዳታን ወአቤሮን እሙንቱ እለ ወረዱ አብቀወተ ምድር ወውኅጠቶሙ፡፡ ዘኁ ፲፮ ፥ ፴፫

፬ ወእመሂ ትብሉ ኢሞተ ክሕድ ክሙ ትንሣኤ፡፡ወእመሂ አልቦ ትንሣኤ አልቦ ዐሪግ፡፡ወእመሂ አልቦ ዐሪግ አልቦ ነቢር በየማነ አብ አልቦ ተስፋ ለመሀይምናን፡፡ትንቢተ ነቢያትኒ አሕሶክሙ ወትምህርተ ሐዋርያትኒ አብጠልክሙ፡፡ወእመሰኬ ወረደ ሥጋሁ ውስተ ሲኦል በእንተ ሥጋ መኑ ሰአለ ዮሴፍ ኀበ ጲላ ጦስ ከመ ያብሖ ለአውርዶ፡፡ወበድነ መኑ ጠብለለ ኒቆዲሞስ በልብሰ ገርዜን ወወደዮ ውስተ መቃብር፡፡ ዮሐ ፲፱ ፥ ፴፰-፴፱

፭ ወእመሰኬ ትቤ ኢተፈልጠ ነፍሱ እምሥጋሁ ክሕድከ ሞቶ ዘይቤ ወንጌላዊ ወሰረቦ ብሒአ ወይቤ ተፈጸመ ኲሉ ወግዒሮ

## ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

## የዓርብ ስቅለት የመኝታ ጊዜ

## ምንባብ

፩ ሦስትነቱ በማይነጠል ባሕርዩ በማይለወጥ የማትታይ የሰውን ልጅ ነፍስ በእጅ በሚነጥቃት የሞቱ በሚነሡም ጊዜ ዳግመኛ ወደ ሥጋ አዳራሽ በሚመልሳት የፀሐይና የጨረቃን አካሄድ ወደ ምዕራብ በሚመልስ የወይራውን ዛፍ በሚነቅለው የተቀጠቀጠውንም ሸንበቆ በሚያጸናው በውጭ ያለውን በሚያስገባ በውስጥ ያለውንም በሚያስወጣ በእግዚአብሔር ስም በሁሉ ላይ የሠለጠነ ነውና ለእርሱ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን አሜን፡፡

፪ በነፍስና በሥጋ ወደሲኦል ወረደ ያሉ አርሲስ የተባሉ የመናፍቃንን ዘለፋ እንናገር ዘንድ ከስንፍና ሽልብታ ራሳችንን እናንቃ፡፡

፫ ስነፎች ምክርና ኅሊናንም ያጣችሁ ሆይ ስለዚህ የስሕተታችሁ ስንፍናም የመጻሕፍት ምስክርነት ያሻልን፡፡ እስኪ እናንተ ራሳችሁ አስቀድማችሁ ንገሩን የእግዚአብሔርን ልጅ ሞተ ትሉታላችሁን ወይስ አልሞተም፡ ሞተ የምትሉት ከሆነ እንደምን በነፍስና በሥጋ ወደሲኦል ወረደ በሕይወት ሳሉ በነፍስና በሥጋ ወደ ሲኦል የወረዱትስ ዳታንና አቤሮን ናቸው ምድር አፏን ከፍታ ውጣቻቸዋለችና፡፡ ዘኁ ፲፮ ፥ ፴፫

፬ አልሞተም የምትሉ ከሆነ መነሣትን ካዳችሁ መሞት ከሌለ መነሣት የለምና መነሣትም ከሌለ ማረግ የለም ማረግም ከሌለ በአብ ቀኝ መቀመጥ የለም ለምእመናንም ተስፋ አይኖርም፡፡ የነቢያትን ትንቢት አሳበላችሁ የሐዋርያትንም ትምህርት አበላሻችሁ ሥጋ ወደ ሲኦል ከወረደ ዮሴፍ ለማውረድ ይፈቅድለት ዘንድ ስለማን ሥጋ ጲላጦስን ለመነ፡ ነቆዲሞስስ የማንን በድን በአዲስ በፍታ ጠቅልሎ በመቃብር አኖረ፡፡ ዮሐ ፲፱ ፥ ፴፰-፴፱

፭ ነፍሱ ከሥጋው አልተለየም ካልህም ወንጌላዊ ሆምጣጤውንም ጉርጉጭ አድርጎ ሁሉ ተፈጸመ አለ በታላቅ ድምጽም ጮሆ ሞተ ያለውን ሞቱን ካድህ፡፡ ሌላውም ወንጌላዊ

ሞት፡፡ወይቤ ካልዕኒ ወንጌላዊ አማኅፀነ ነፍሰ
ኀበ አቡሁ ወይቤ አባ ውስተ እዴከ አማኅፅን
ነፍስየ ወዘንተ ብሂሎ ሞተ፡፡ማቴዎስኒ ይቤ
ወጸርኀ እግዚእ ኢየሱስ በዐቢይ ቃል ወወ
አት መንፈሱ ሶቤሃ፡፡ዮሐንስኒ ይቤ ወአፅነነ
ርእሶ ወወፅአት መንፈሱ፡፡ናሁኬ ፀአተ መንፈ
ሱ ተጽሕፈ በእደ አርባዕቱ ወንጌላውያን፡፡
ዘከመ እፎ ይትከሀለከ ከመ ትክሐድ ፀአተ
ነፍሱ እምሥጋሁ፡፡ ማቴ፳፯+፵፰ ማር፲፭+፴፯

፮ ነፍሱሰ እምከመ ወፅአት እምሥጋሁ
ወረደት ውስተ ሲኦል ምስለ ኀይለ መለኮት
ጊዜ ፱ ሰዓት ወአውፅአቶሙ ለነፍሳተ ጻድቃን
ወአብአቶሙ ውስተ ገነት ትፍሥሕት ምስለ
ነፍሰ ፈያታይ ዘወሀቦ ኪዳነ በዲበ ዕፀ
መስቀል እንዘ ይብል አመን ፈድፋደ ከመ
ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት፡፡ ሉቃ፳፫+፵፫

፯ አበውሰ ነቢያት አመኒ ነበሩ ውስተ
ሲኦል በነፍሳቲሆሙ ነበሩ ወአኮ ምስለ
ሥጋሆሙ በከመ ተርጐሙ ሐዋርያት በእንተ
ቃለ መዝሙር ዘይቤ እስመ ኢተኃድጋ ውስ
ተ ሲኦል ለነፍስየ፡ወኢትሁብ ለጻድቅከ ይርአ
ይ ሙስና፡ወአርአይከኒ ፍኖተ ሕይወት፡ወአ
ጽ ገብከኒ ሐሤተ ምስለ ገጽከ፡ወትፍሥሕት
ውስተ የማንከ ለዝሉፉ፡፡ታበውሑነሁ ንንግር
ክሙ ክሡተ በእንተ ዳዊት አበ ቀደምት ዘከ
መ ሞተ ወተቀብረ ወኀቤነ ሀሎ መቃብሪሁ
እስከ ዮም፡፡ መዝ፲፭+፲ ሐዋ፪+፳፭- ፴፭

፰ ሰምዑ እንከ ኦ አብዳን ዘከመ ይቤሉ
ሐዋርያት ወኀቤነ ሀሎ መቃብሪሁ ለዳዊት
እስከ ዮም፡፡ወአመሰ ሐዋርያት ወሀቡነ ምክ
ንያተ በእንተ ዳዊት መቃብሪሁ ንሕነኒ ናስ
ተማፅእ ለከ ከማሁ አለ ተቀብሩ አብርሃም
ይስሐቅ ወያዕቆብ በምድረ ከነአን ውስተ
በዐተ ካዕበት ዘገራህተ ኤፌሮን ኬጥያዊ፡፡
ወለዮሴፍኒ ተወሰከ አዕጽምቲሁ ህየ፡፡ወሙሴ
ኒ ሞተ በምድረ ናባው ዘሞአብ ወተቀብረ ቅሩ
በ ቤተ ብዔልፌጎር ፡፡ወአሮንኒ በደብረ ሆር
በገቦ ምድረ ኤዶም፡፡ዳዊትኒ በቤተ ልሔም
ወኢሳይያስኒ ወኤርምያስ በምድረ ይሁዳ፡፡
ዳንኤልኒ ወሕዝቅኤል በምድረ ባቢሎን፡፡ወ፫
ደቂቅኒ በምድረ ከለዳውያን ቅሩበ መቃብሪሁ
ለናብክድናጾር፡፡ ዘፍ፳፭+፱ ፣፶+፲፫ ዘዳ፴፬+፭

፱ ወኤልሳዕኒ በደብረ ሰማርያ፡፡ ወቦ
ባዕዳንኒ ነቢያት እለ ተቀብሩ በኀበ ከፈሎሙ

አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ ብሎ
ነፍሱን ለአባቱ አደራ አስጠበቀ ይህንንም
ተናግሮ ሞተ አለ፡፡ ማቴዎስም ጌታ ኢየሱስም
በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱም ያን ጊዜ ወጣች
አለ፡፡ ዮሐንስም ራሱን ዘንበል አደረገ ነፍሱም
ወጣች አለ፡፡ እነሆ የነፍስ መውጣት በአራቱም
ወንጌላውያን ተጽፏል፡ እንግዲህ አንተ የነፍሱን
ከሥጋው መወጣት ትክድ ዘንድ እንደምን ይቻ
ልሀል፡፡ማቴ፳፯+፵፰ ማር፲፭+፴፯ ሉቃ፳፫+፵፮
ዮሐ፲፱+፴

፮ ነፍሱስ ከሥጋው ከወጣች ዘንድ
በዘጠኝ ሰዓት ከመለኮት ኃይል ጋር ወደ ሲኦል
ወረደች የጻድቃንንም ነፍሶቻቸውን አወጣቻቸው
ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት እንደምትኖር አብዝተህ
እመን ብሎ በዕፀ መስቀል ላይ ቃል ኪዳን
ከሰጠው ከቀማኛው ነፍስ ጋር ወደ ደስታ ገነት
አስገባቻቸው፡፡ ሉቃ፳፫+፵፫

፯ አባቶች ነቢያትስ በሲኦል ቢኖሩም
በነፍሳቸው ኖሩ ከሥጋቸው ጋር ግን
አይደለም፡፡ ሐዋርያት ነፍሴን በሲኦል አት
ተዋትምና ጻድቅህንም ጥፋትን ያይ ዘንድ
አትሰጠውም የሕይወትን ጐዳና አሳየኸኝ በፊ
ትህም አጠገብኸኝ ደስታም ዘወትር በቀኝህ ነው
ያለውን የመዝሙር ቃል የቀደሙ ሰዎች አባት
ስለሆነ ስለዳዊት እንደሞተና እንደተቀበረ
መቃብሩም እስከዛሬ ድረስ በእኛ ዘንድ እንዳለ
በግልጥ እንነግራችሁ ዘንድ ትፈቅዱልናላችሁን
ብለው እንደተረጐሙ፡፡ መዝ፲፭+፲ሐዋ፪+፳፭- ፴፭

፰ ሰነፎች ሆይ እሽግዲህስ ሐዋርያት የዳዊት
መቃብር እስከ ዛሬ ድረስ በእኛ ዘንድ አለ
እንዳሉ ስሙ፡ ሐዋርያት የዳዊትን መቃብር
ምክንያት ካደረጉለንስ እኛም እንደነርሱ ያለውን
እናመጣልሀለን፡፡ አብርሃምና ይስሐቅ ያዕቆብም
በከነአን ምድር በኬጥያዊው ኤፌሮን እርሻ ላይ
በምትገኝ ሁለት ክፍሎች ባሏት መቃብር
ተቀበሩ፡ የዮሴፍም አጥንቶች በዚያም
ተጨመሩ፡፡ ሙሴም የሞአብ ዕፃ በሆነ በናባው
ተራራ ሞተ በብዔልፌጎርም አቅራቢያ ተቀበረ
አሮንም በኤዶም ምድር አጠገብ በሆር ምድር
ተቀበረ፡፡ ዳዊት በቤተልሔም ኢሳይያስና
ኤርምያስም በይሁዳ ምድር ዳንኤልና ሕዝቅኤል
በባቢሎን ምድር ተቀበሩ ሦስቱ ሕፃናትም
በናቡከደነጾር መቃብር አቅራቢያ በከለዳውያን
ምድር ተቀበሩ፡፡ ዘፍ፳፭+፱ ፣፶+፲፫ ዘዳ፴፬+፭

፱ ኤልሳዕም በሰማርያ ተራራ
ተቀበረ የእግዚአብሔር ፈቃድ ባደላቸውም ቦታ

www.ethiopianorthodox.org

ሥምረተ እግዚአብሔር፡ወኀጣእኩ ዘይዜን ወኢ በእንቲአሆሙ፡፡ወአዳምሂ አበ ኲልነ ተቀብረ በምድረ ኤልዳ እንተ ይእቲ መካነ ፍጥረቱ፡፡ወላዕለ መቃብሪሁ ተተክለ ዕፀ መስቀል በሥምረተ እግዚአብሔር ወላዕሌሁ ተክዕወ ደመ መሲሑ ለአብ ወማየ ምንዛሕ ዘርግዘት ገቦሁ፡፡ ማይሰ ዘውኀዘ እምገቦ መሲሑ ለእግዚአብሔር ወተከዕወ ላዕሌሁ ለአዳም ወአጥመቆ ከመ ያብኦ ዐቢየ ክርስቲያን፡፡ ወደመ መለኮቱኒ ዘተሠውጠ ኀበ መቃብሩ ኮነ ለሥርዓተ ምሥጢር ዘሐዲስ ቍርባን፡፡ በድነ ካህን ተረግዘ ገቦሁ በኲናተ ሐራዊ፡፡ ወበማይ ዘውሕዘ እምነ ገቦሁ አጥመቆሙ ለአብድንተ ትካት፡፡ወአብድንተ መሀይምናን ወፅኡ እመቃብሪሆሙ ወዘለፍዎሙ ለሰቃልያን፡፡ በድነ ካህን አስተሳተፎሙ ለአብድንት በደመ መለኮቱ፡፡ለአብድንተ መሀይምናን ተቀደሱ በምሥጢረ ቅድሳቲሁ፡፡በድነ ካህን ዓተቦሙ ለአብድንት በጽላሎተ መስቀሉ፡፡ ወአብድንተ መሀይምናን ነሚኦሙ ማዕተበ ጸጋ ቦኡ ውስተ ሀገር ቅድስት፡፡

፲ በቀራንዮ ተገብረ ሥርዓተ ምሥጢር በኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ለሊሁ ቍርባን ወመስቀሉ ምሥዋዕ፡፡ለሊሁ ካህን ወሥጋሁ ኅብስተ ሕይወት፡፡ለሊሁ በድን ወመለኮቱ ሕያው፡ለሊሁ ቅሡፍ ወመለኮቱ ኢልኩፍ፡፡ለእለ ውስተ መቃብር ገብረ ሎሙ ሕይወት በማይ ወደም ዘውሕዘ እምበድነ ሥጋሁ ወለእለ ውስተ ሲኦል ሰበከ ሎሙ ግዛዕነ በነፍሱ፡፡ ወሥጋሁሰ ቅድስት እንተ ረገዝዋ በኲናት ኢያስተንፈሰት ወእንዘ ይገንዝዋ በመዋጥሐ ገርዜን ወኢተሐውሰት እስመ ዕርቅተ ኮነት እምህላዌ ነፍሱ፡፡በከመ ኢቦአት ነፍሱ ምስለ ሥጋሁ ውስተ መቃብር ከማሁ ኢወረደት ሥጋሁ ውስተ ሲኦል፡፡ወእመሂ ትቤ ምስለ ነፍሱኒ ወረደት ሥጋሁ ውስተ ሲኦል፡፡ወውስተ መቃብርኒ ቦአት እንበለ ነፍስ ወአነሂ እብለከ ቦኑ ምንታዌ ለሥጋዌ ከመ ያስተርኢ ኀበ ፩ ገጸ መካን ፩ በከዊነ በድን ወ፩ በመንፈሰ ሕይወት፡፡

፲፩ እመንኬ አ ረሲዕ ከመ እልቦቱ ለክርስቶስ ክልዔ ሥጋ ፩ ዘይመውት ወ፩ ዘኢይመውት፡፡ጳውሎስኒ ይቤ ወበነፍስተ ሥጋሁ ለአዳም ወረደ ውስተ ሲኦል፡፡ አእምርኬ አ አብድ ከመ ኢይቤ በሥጋሁ ዘእንበለ ዳእሙ በነፍስተ ሥጋሁ፡፡ በነፍስተ ሥጋሁሰ

የተቀበሩ ሌሎች ነቢያትም አሉ፡፡ ስለነርሱ ግን የሚነግረኝ አጣሁኝ የሁላችን. አባት አዳም በተፈጠረባት ሥፍራ በኤልዳ ምድር ተቀበረ፡፡ በመቃብሩም ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዕፀ መስቀል ተተከለ በርሱም ላይ የአብ መሢሕ ደም በጐኑም መወጋት የወጣ የማጥመቂያ ውኃ ፈሰሰ፡ ከእግዚአብሔር መሢሕ ጐን የፈሰሰውም ውኃ በአዳም ላይ ፈሰሰ፡ ታላቅ ክርስቲያንም ሊያደርገው አጠመቀው ወደ መቃብሩ የተረጨ የመለኮቱም ደም ለአዲስ ቁርባን ምሥጢር ሥርዓት ሆነ፡፡ የካህኑ በድን በጭፍራ ጦር ጐኑን ተወጋ ከጐኑም በፈሰሰው ውኃ የቀድሞ ጊዜ በድኖችን አጠመቃቸው የምእመናን በድኖችም ከመቃብሮቻቸው ወጥተው ሰቃዮችን ዘለፉአቸው፡፡ የካህኑ በድን በመለኮቱ ደም በድኖች አንድ አደረጋቸው የምእመናን በድኖች በቅድስናው ምሥጢር ተቀደሱ፡ የካህኑ በድን በመስቀል ጥላ በድኖችን ባረካቸው የምእመናንም በድኖች የጸጋ ማኅተም ተቀብለው ወደ ቅድስት ሀገር ገቡ፡፡

፲ በቀራንዮ የምሥጢር ሥርዓት በኢየሱስ ክርስቶስ ተደረገ እርሱ ቁርባን መስቀሉም መሠዊያ እርሱ ካህን ሥጋውም የሕይወት እንጀራ ሆነ እርሱ በግ ደሙም ወይን እርሱ በድን መለኮቱም ሕያው እርሱ የተገረፈ በመለኮቱ የማይዳሰስ ነው በመቃብር ለነበሩት ከሥጋው በድን በፈሰሰ ውኃና ደም ሕይወትን ሰጣቸው፡ በሲኦል ለነበሩትም በነፍሱ ነፃነትን ሰበከላቸው በጦር የወጉአት ክብርት ሥጋው ግን አልተነፈሰችም፡በበፍታ ሲገንዙአትም አልተንቀሳቀሰችም፡ ከነፍሱ ባሕርይ የተለየች ሆናለችና ነፍሱ ከሥጋው ጋር ወደመቃብር እንዳልገባች እንዲሁ ሥጋው ወደ ሲኦል አልወረደችም ከነፍሱም ጋር ሥጋ ወደ ሲኦል ወርዳለች ካልህም እኔም እንጂ ወደ መቃብርም ያለ ነፍስ ገባች እልሀለሁ፡፡ በአንዱ በድን በአንዱም የሕይወት መንፈስ ሆኖ በሁለት ሥፍራ ይታይ ዘንድ ለሥጋ ሁለትነት ይቻለዋልን፡፡

፲፩ ዝንጉ ሆይ ክርስቶስ አንዱ የሚሞት አንዱም የማይሞት ሁለት ሥጋ እንደሌለው እመን፡፡ ጳውሎስም በአዳም ሥጋ ነፍስ ወደሲኦል ወረደ አለ፡፡ ሰነፍ ሆይ በሥጋው ነፍስ እንጂ በሥጋው እንዳላለ ዕወቅ፡፡ በሥጋውም ነፍስም ማለት በአዳም ሥጋ ውስጥ በነበረች ነፍስ ማለት ነው የአዳም ሥጋ ግን

www.ethiopianorthodox.org

ብሂል በነፍስ እንተ ነበረት ኀበ ሥጋ አዳ ም፡፡ወሥጋ አዳምሰ ውእቱ ሥጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ እምወለተ አዳም፡፡እስመ ብዙኃን እለ ስሕቱ በእንተ ቃል ዘጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ኪዳን ዘይቤ ወእንዘ ይወርድ በሥጋ ጌገዮ ወአም ሰሎ በከመ ያለምድ ውኂጠ፡፡ወሶበ ርእየ በላዕሌሁ ኃይለ መለኮቱ ጸርገ መልአከ ሞት ወይቤ አይ ውእቱ ዝንቱ ዘእምሥልጣንየ ሥጋ ለቢሶ ዘሞአኒ፡ አይ ውእቱ ዘምድረ ለብሰ ውእቱሰ ሰማያዊ ውእቱ፡፡

፲፪ ዘንተ ተረጕሙ ዕንቡዛነ ልብ በእንተ ርደቱ ውስተ ሲኦል በሥጋ፡፡ አኮ ከመዝ ፍካሬሁሰ እስመ ዘቀዲሙ ይቤ በእንተ መለኮቱ አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ፡፡ ካዕበመ ይቤ በእንተ ትስብእቱ አባ አኀ ልፉ እምኔየ ለዛቲ ሰዓት፡፡ ናሁኬ ርደተ ቃል እምዕበየ መለኮት ኀበ ትሕትና ትስብእት፡፡ ደገመ ወይቤ ሰብሐኒ አባ በሰብሐቲከ ዘሀሎ ምስሌከ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፡፡ ወካዕበመ ይቤ በከመ አብ ሕያው አነኒ ሕያው በእንተ አብ ዘንተ ዘይቤ እንዘ ያዔሪ ርእሶ ምስለ አቡሁ በእንተ ዕበየ መለኮቱ፡፡ወበቃለ ትሕትና ዘፍና ትስብእት ይቤ አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወለምንት ኀደገኒ፡፡ወሶበ ሰምዐ ዘንተ መልአከ ሞት አምሰሎ ከመ ዘያለምድ ውሒጠ፡፡ምንት ውእቱ ዘለመደ ውሒጠ ዘእንበለ ዳእሙ ነፍሰ ጻድቃን እለ አወፈዮሙ ለሲኦል፡፡

፲፫ ወሶበ ርእዮ ለእግዚእ ኢየሱስ ቅሡለ በመቅሠፍተ ጥብጣቤ ወጽዑረ በቅን ዋተ መስቀል አምሰሎ ከመ ያለምድ ውሒጠ ፡፡ወሶበ ይቤ አባ አኅልፉ እምኔየ ለዛቲ ሰዓት ረስዐ ቃለ ዘይቤ አነ ወአብ ፩ ንሕነ፡፡ወበዝ ጌገዮ ወአምሰሎ ከመ ዘያለምድ ውሒጠ፡፡ ወሶበ ሰምዐ እንዘ ይብል አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወለምንት ኀደገኒ ረስዐ ቃለ ዘይቤ ወበከመ አብ ሕያው አነሂ ሕያው በእንተ አብ ወበዝ ጌገዮ ወአምሰሎ በከመ ያለምድ ውሒ ጠ፡፡ወሶበ ርእየ ኀሳር በዲበ ዕፀ መስቀል ረስዐ መንክራቲሁ ዘገብረ በላዕለ ድውያን ወበዝኒ ጌገዮ ወአምሰሎ በከመ ያለምድ ውሒጠ፡፡

፲፬ ወሶበ ርእየ ተወርዶ ዕበየ መለኮት ኀበ ትሕትና ሥጋ ወበዝ ጌገዮ ወአምሰሎ በከመ ያለ ምድ ውሒጠ፡፡ዘለመደ ውሒጠ ነፍሳተ አብቀወ አፋሁ ከመ የሐጥ ነፍሶ ለጻድቅ ወበአብቅዎ ከናፍሪሁ ወፅአ አሕጻ እሳት እም ጕንጸ መለኮት

ከአዳም ሴት ልጅ የነሣው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ነው በኪዳን መጽሐፍ በሥጋም ሲወርድ መዋጥን እንዳስለመደ አስመስሎ ሸንገለው በእርሱም ላይ የመለኮቱን ኃይል ባየ ጊዜ የሞት መልአክ ጮኸ ከሥልጣኔ ያልሆነ ሥጋንም ለብሶ ድል የነሣኝ ይህ ማን ነው አለ፡ ምድራዊውን የለበሰ እርሱ ግን ሰማያዊ የሆነ ማን ነው ተብሎ ስለተጻፈው ቃል የሳቱ ብዙዎች ናቸውና፡፡

፲፪ ልባቸው የጠፋ ይህን በሥጋ ወደ ሲኦል ስለመውረድ ተረጐሙት ትርጉሙ ግን እንዲህ አይደለም፡ እርሱ ስለ መለኮት አስቀድሞ እኔና አብ አንድ ነን ብሎ የተናገረ ነውና፡፡ ዳግመኛም ስለ ሰውነቱ አባት ሆይ ይህችን ሰዓት ከእኔ አርቃት አለ፡፡ የቃል ከመለኮት ክብር ሰው ወደ መሆን ትሕትና መውረድ እነሆ ደግሞም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ከአንተ ጋር ባለ ክብርህ አክብረኝ አለ ሁለተኛም አብ ሕያው እንደሆነ እኔም የአብ ልጅ ስለሆንሁ ሕያው ነኝ አለ፡፡ ይህንን የተናገረው ስለ መለኮቱ ክብር ራሱን ከአባቱ ጋር ሲያስተካክል ነው ሰው በመሆኑ አንገርም በትሕትና ቃል አምላኬ አምላኬ እየኝ ስለምንስ ተውኸኝ አለ፡፡ የሞት መልአክም ይህንን ሰምቶ መዋጥን እንዳስለመ ደው መሰለው፡፡ ለሲኦል የሰጣቸውን የጻድቃንን ነፍሳት እንጂ መዋጥ የለመደው ምንድር ነው፡

፲፫ ጌታ ኢየሱስን በጅራፍ ገረፉት ቆስሎ በመስቀሉም ችንካሮች ተጨንቆ ባየው ጊዜ መዋጥን እንደለመደው መሰለው አባት ሆይ ይህች ሰዓት ከእኔ አርቃት ባለ ጊዜ እኔና አብ አንድ ነን ያለውን ቃል ዘነጋው በዚህም መዋጥን እንደለመደው መስሎት በደለው፡ አምላኬ አምላኬ እየኝ ስለምንስ ተውኸኝ ሲል አብ ሕያው እንደሆነ እኔም የአብ ልጅ ስለሆንሁ ሕያው ነኝ ያለውን ቃል ረሳ፡፡ በዚህም መዋጥን እንደለመደው መስሎት በድፍረት ቀረበው፡፡ በዕፀ መስቀል ላይ ተጕሳቁሎ ባየው ጊዜ በበሽተኞች ላይ ያደረጋቸውን ድንቆቹን ዘነጋ በዚህም መዋጥን እንደለመደው መስሎት በድፍረት ቀረበው፡፡

፲፬ የመለኮትን ክብር ወደ ሥጋ ትሕትና መወረድ ባየ ጊዜ በዚህም መዋጥን እንደለመደው መስሎት ሳተው፡፡ ነፍሳትን መዋጥ የለመደ የጻድቁን ነፍስ ይውጥ ዘንድ አፉን ከፈተ ከንፈሮቹንም በማላቀቅ ከመለኮት

www.ethiopianorthodox.org

ወቦአ ውስተ ጕርጔሁ ለዘያለምድ ውሒጠ፡፡
ወእምዝ ጸርኀ መልአከ ሞት ወይቤ አይ
ውእቱ ዝንቱ ዘእምሥልጣንየ ሥጋ ለቢሶ
ዘሞዐኒ አይ ውእቱ ዝንቱ ዘምድረ ለብሰ፡፡
ናሁኬ መዋዒ ተሞዐ ወነዐዊ ተንዕወ ወአስ
ጋሪ ተሠግረ፡እስመ ውእቱ ኮነ ዘይትሜጠ
ነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን እምነ ሥጋሆሙ፡፡

፲፩ ወአልቦ ዘአሕመመቶ አሐቲ ነፍስ
እምእላንቱ ዘእንበለ ነፍሰ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዘውስቴታ ኃይለ መለኮት፡፡ወበ እንተዝ ጸርኀ
መልአከ ሞት ወይቤ ውእቱሰ ሰማያዊ ውእ
ቱ፡፡ወለነቢያትኒ ቀደምት ይትሜጠ ነፍሳቲ
ሆሙ ወአብድንቶሙሰ ይትኀደግ ለተዝካረ
ዝህር፡፡ወለእግዚእነሂ መሠጠ ነፍሶ እምሥጋ
ሁ ከመ ይደያ ውስተ ዓጸደ ደይን፡፡ወበቈላተ
ደይን አድወዮ በኃይለ መለኮቱ፡፡ ወበርበረ
ነፍሳተ ጻድቃን እለ ሀለዉ ህየ ወአውፅኦሙ
እምህየ ወአብኦሙ ውስተ ገነት ፍና ሰርክ
በዕለተ ዓርብ በሳብዕ ዓም ወከማሁ ቦአ፡፡ ውስ
ተ ገነት ፍና ሰርክ ዘዓርብ ፋሲካ፡፡
፲፪ ወበእንተ ፀአቱ እምገነት ትብል
ቅድስት ኦሪት ወአንሶሰወ እግዚአብሔር ውስ
ተ ገነት ፍና ሰርክ፡፡ወሰምዑ አዳም ወብእሲ
ቱ እንዘ ያንሶሱ ውስተ ገነት ወተኀብኡ አዳ
ም ወብእሲቱ ማእከለ ዕፀዊሃ ለገነት፡፡ወይቤሎ
እግዚአብሔር ለአዳም አዳም አይቴ ሀለውከ፡፡
ወይቤ አዳም ቃለከ ሰማዕኩ እንዘ ታንሶሱ
ውስተ ገነት ወፈራህኩ ወተኃባእኩ እስመ ዕራ
ቅየ አነ፡፡ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም
መኑ አይድዐከ ከመ ዕራቀከ አንተ ሶበ አኮ
ዘበላዕከ ዘንተ ዕፀ ዘአነ ከላእኩከ፡፡ ወይቤ
አዳም ብእ ሲትየ እንተ ወሀብከኒ ትንበር
ምስሌየ ይእቲ ወሀበተኒ ወበላዕኩ፡ወይቤላ
እግዚአብሔር ለብ እሲት ዘንተኑ ገበርኪ
ወትቤ ሔዋን አርዌ ምድር አስፈጠተኒ
ወይቤላ እግዚአብሔር ለአርዌ ምድር
ርግምት ኩኒ እምኵሉ አራዊተ ምድር በእን
ግድዓኪ ሑሪ ወመሬተ ብልዒ ወኵሎ መዋዕ
ለ ሕይወትኪ አስተጻርር ማእከሌኪ ወማእከለ
ብእሲት ማእከለ ዘርእኪ ወማእከለ ዘርኣ
ውእቱ ለይዕቀብ ርእሰኪ ወአንቲኒ ዕቀቢ
ሰኰናሁ፡፡ወአውፅኦሙ እግዚአብሔር ለአዳም
ወለብእሲቱ እምገነት ተድላ፡፡ ዘፍ፫፥፰-፲፱
፲፫ ወበዝ አእመርነ ከመ ፍና ሰርክ
ወፅአ አዳም እምገነት ወካዕበ ፍና ሰርክ ገብአ

ሰገባ የእሳት ሾተል ወጥቶ መዋጥ በለመደው
ጉሮሮ ገባ፡፡ ከዚህም በኋላ የሞት መልአክ
ከሥልጣኔ ያልሆነ ሥጋን ለብሶ ድል የነሣኝ
ይህ ማን ነው ምድራዊውን ሥጋ የለበሰ ይህ
ማን ነው ብሎ ጮኸ፡፡ እነሆ አቸናፊው ተቸነፈ
አዳኙም ታደነ አጥማጁም ተጠመደ የጻድቃንን
ነፍሶቻቸውን ከሥጋቸው የሚቀበል እርሱ
ነበርና፡፡

፲፩ የመለኮት ኃይል ከኢየሱስ
ክርስቶስ ነፍስ በቀር ከእነዚያ መካከል
የሠቀየችው አንዲት ነፍስ እንኳ የለችም፡፡
ስለዚህም የሞት መልአክ ይህ ግን ሰማያዊ ነው
ብሎ ጮኸ የቀደሙ ነቢያትንም ነፍሶቻቸውን
ይቀበላል በድኖቻቸው ግን ለመቃብር መታሰቢያ
ይቀራል፡፡ የጌታችንንም ነፍሱን እንጦርጦስ
ይጨምራት ዘንድ ነጠቀ በደይን ቀላዮችም
በመለኮቱ ኃይል ሠቀየው በዚያም የነበሩትን
የጻድቃንን ነፍሶች በረበረ፡፡ ከዚያም አውጥቶ
በሠርክ ጊዜ ወደ ገነት አስገባቸው አዳም
በሠርክ ጊዜ በዓርብ ቀን በሰባተኛው ዓመት
እንደወጣ እንዲሁ በፋሲካ ዓርብ በሠርክ ጊዜ
ወደ ገነት ገባ፡፡

፲፪ ከገነት ስለመውጣቱ የከበረች ኦሪት
በሠርክ ጊዜም እግዚአብሐር በገነት ተመላለሰ፡
አዳምና ሚስቱም በገነት ሲመላለስ ሰምተው
በገነት ዛፎች መካከል ተደበቁ፡ እግዚአብሔርም
አዳምን አዳም ወዴት አለህ አለው አዳምም
በገነት ስትመላለስ ድምፅህን ሰምቼ ፈራሁ
ተሸሸግሁም ራቁቴን ነኝና አለ፡ እግዚአብሔርም
አዳምን ራቁትህን እንደሆንህ ማን ነገረህ እኔ
የከለከልሁህን ይህን እንጨት ስለበላህ
አይደለምን አለው፡፡ አዳምም ከእኔ ጋር
እንድትኖር የሰጠኸኝ ሚስቴ እርሷ ሰጥታኝ
በላሁ አለ፡፡ እግዚአብሔርም ሴቲቱን ይህን
አደረግሽን አላት ሔዋንም እባብ አሳተችኝ
አለች እግዚአብሔርም እባብን ከምድር
አራዊት ሁሉ መካከል የተረገምሽ ሁኚ በደረትሽ
ሂጂ ትቢያም ተመገቢ በሕይወት ዘመንሽም
ሁሉ በአንቺና በሴቲቱ በዘርሽና በዘሯ መካከል
ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስሽን
ይጠብቃል አንቺም ተረከዙን ትጠብቂያለሽ
አላት፡፡ እግዚአብሔርም አዳምና ሔዋንን
ከተድላ ገነት አስወጣቸው አለች፡፡ ዘፍ፫፥፰-፲፱

፲፫ በዚህም አዳም በሠርክ ጊዜ ከገነት
እንደወጣ ዐወቅን ዳግመኛም በሠርክ ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

ውስተ ገነት፡፡እስመ በ፱ ሰዓት ይቤሎ እግዚእነ ለፈያታይ እመን ፈድፋደ ከመ ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት፡፡ ወበይእቲ ሰዓት ወፅአት መንፈሱ ለእግዚእ ኢየሱስ፡፡ ወለ ፈያታይስ በ፲ወ፩ ሰዓት ወፅአት መንፈሱ ሶበ ሰበርዎ ቊይጾ በከመ ጽሑፍ ውስተ ሲኦል ለመድኃኒነ ወአውፅአቶሙ ለነፍሰ አዳም ወለ ደቂቁ ወአብ አቶሙ ውስተ ገነት ጊዜ ፲ወ፩ ምስለ ነፍሰ ፈያታይ ዘየማን ዘወሀቦ ኪዳነ በዲበ ዕፀ መስቀል ተርኅወት አንቀጸ ምሕረቱ ለእግዚአብሔር ወበጠለ ኲናተ እሳት እምእደ ሱራፌል ወሰይፈ እሳትኒ እምእደ ኪሩቤል፡፡ ተርኅወ አንቀጸ ገነት ወቦኡ መራዕይ ውስተ መርዔቶሙ፡፡

ወደ ገነት ተመለሰ በዘጠኝ ሰዓት ጌታችን ቀማኛውን ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት እንደምትሆን አብዝተህ እመን ብሎታልና በዚያችም ሰዓት የጌታ ኢየሱስ ነፍስ ወጣች፡፡ የቀማኛው ነፍስ ግን በዮሐንስ ወንጌል እንደተጻፈ ጭኑን በሰበሩት ጊዜ በአሥራ አንደኛው ሰዓት ነፍሱ ወጣች በዘጠኝ ሰዓት የመድኃኒታችን ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዳ የአዳምንና የልጆቹን ነፍስ አወጣቻቸው በአሥራ አንድ ሰዓትም በዕፀ መስቀል ላይ ሳለ ቃልኪዳን ከሰጠው በቀኝ ከተሰቀለው ሽፍታ ነፍስ ጋር ወደገነት አስገባቻቸው የእግዚአብሔር የምሕረቱ ደጃፍ ተከፈተች የእሳት ጦርም ከሱራፌል እጅ የእሳት ሰይፍም ከኪሩቤል እጅ ጠፋ የገነት ደጃፍ ተከፈተ በጎችም ወደ መንጋቸው ተመለሱ፡፡ ሉቃ፳፫፥፵፫ ዮሐ፲፱፥፴፩

፲፯ እንፈርዓጹ ነቢያት ሶበ ርእዩ ዕፀወ መዐዛ ዘዘዚአሁ አርአያሁ ወዘዘዚአሁ ኅብሩ ጽጌሁ ወዘዘዚአሁ አስካለ ፍሬሁ፡፡ በማየ ገነትኒ ንጹሕ ከመ ሐሊብ ወጥዑም ፈድፋደ እምጸቃውዐ መዐር፡፡ ርእዩ እንዘ ይሠውጥ አሐዱ በዲበ ካልኡ ወእንዘ ይውሕዝ ፩ እምለፌ ወ፩ እምለፌ፡፡ወርእዩ ወሐይዝተ ብርሃን ወሥነ ዘያጸደለድል፡፡ወርእዩ አፍላገ ትፍሥሕት ወሐሤት እንዘ ያንበሐብሑ በኃይል ማእከለ ዕፀዊሃ ለገነት፡፡ጸገቡ እንበለ ይብልዑ ወረወዩ እንበለ ይስትዩ፡፡ሰከሩ እምርእየ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ወአኮ እምሰሪበ ሜስ፡፡ሰከሩ እምፍሥሓ እምወይን፡፡ሰከሩ በለ ብዎ ወጥበብ ወአኮ በአንኰልዎ ወበዕንባዜ፡፡

፲፯ መልካቸው የተለያየ የአበቦቻቸውም ቀለም የተለያየ ሽታቸው የተለያየ የፍሬአቸውም ዘለላ የተለያየ የሆኑ መዓዛ ያላቸው ዛፎችን ባዩ ጊዜ በደስታ ዘለሉ የገነትም ውኃ እንደወተት ንጹህ ከማር ወለላም ይልቅ እጅግ የጣፈጠ ነው አንዱ በሌላው ላይ ሲጨመር አንዱ ከዚህ አንዱም ከዚያ ሲፈስ አዩ፡፡ የብርሃን ጉርፎችን የሚያበራም ጸዳልን አዩ፡ የደስታና የሐሤት ወንዞችም በገነት ዛፎች መካከል በኃይል ሲንሾሹ አዩ፡፡ ሳይበሉ ጠገቡ ሳይጠጡም ረኩ ጠላ በመጠታት ያይደለ የእግዚአብሔርን ክብር ከማየት የተነሣ ሰከሩ፡፡ በወይን ያይደለ በደስታ ሰከሩ በማስተዋልና በጥበብ ሰከሩ አእምሮን በመሳት ልብንም በማጣት አይደለም፡፡

፲፰ ወቦ እለ ይብሉ ከመ ኢነበሩ አዳም ወነቢያት ውስተ ሲኦል፡፡እፎኬ ይብልዎሙ ለነቢያት ኢነበሩ ውስተ ሲኦል፡፡በእንተ ምንትኬ ይቤ ዳዊት እስመ ኢተኃድጋ ውስተ ሲኦል ነፍስየ፡ ወኢትሁቦ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና፡፡ እእምሩኬ ከመ ኢይቤ ኢታውርዳ ውስተ ሲኦል ለነፍስየ፡፡ አላ ይቤ እስመ ኢተ ኃድጋ ውስተ ሲኦል ለነፍስየ፡፡እስመ በተአምኖ ነበበ ዘንተ ነቢይ አእሚሮ በመንፈሰ ትንቢት ከመ ይወርድ እግዚእነ ውስተ ሲኦል ከመ ያግዕዝ ነፍሳተ ነቢያት እለ ሀየ ሀለዉ፡፡ ወበእንተዝ ይቤ ኢተኃድጋ ውስተ ሲኦል ለነፍስየ ምስለ ነፍሳተ እለ ያርብሕ እለ ተአሰሩ ሀየ ወምስለ ነፍሳተ አሕዛብ እለ ጌገዩ በአምልኮ ጣዖት፡፡ ወበእንተዝ ተፈሥሐ ነቢይ እንዘ ይሴፎ ፀአተ እምሲኦል ምስ ለ ነፍሳተ ነቢያት ወነገረ ከመ ኢይትኃደግ ውስተ ሲኦል ምስለ ነፍሳተ ኃጥአን፡፡ መዝ፲፭፥፲

፲፰ አዳምና ነቢያት በሲኦል እንዳልኖሩ የሚናገሩ አሉ ነቢያትን እንደምን በሲኦል አልኖሩም ይሉአቸዋል፡ ዳዊት ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ጻድቅህም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም ያለው ስለምንድር ነው ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና አለ እንጂ ነፍሴን ወደ ሲኦል አታውርዳት አላለም፡፡ ነቢዩ ጌታችን በዚያ ያሉትን የነቢያት ነፍሳት አርነት ሊያወጣ ወደ ሲኦል እንደሚወርድ በትንቢት መንፈስ ዐውቆ ይህንን በመታመን ተናግሯልና፡፡ ስለዚህም ነፍሴን በዚያ ከታሠሩ ከአርበኞች ጣዖትም በማምለክ ከበደሉ ከአሕዛብ ነፍሳት ጋር በሲኦል አትተዋትም አለ፡፡ ስለዚህም ነቢዩ ከነቢያት ነፍሶች ጋር ከሲኦል መውጣትን ተስፋ አድርጎ ደስ ተሰኝ ከኃጥአን ነፍሶች ጋር በሲኦል እንደማይቀር ተናገረ፡፡ መዝ፲፭፥፲

www.ethiopianorthodox.org

፳ ጳውሎስኒ ይቤ ወለኢየሱስ ክርስቶስ ሰቀልዎ በሥጋሁ ምስለ ፍትወት ወኃጢአት ምንትኬ ውእቱ ዝንቱ ቃለ ሐዋርያ በኑ ፍትወት በኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወቦኑ ኃጢአት በኀበ ክርስቶስ፡፡ ፈክር ሊተ ኦ አቡየ ጳውሎስ ዘንተ ምሥጢረ ቃልከ፡፡ወእመ አኮሰ ባርክ ላዕሌየ ከመ ይርድአኒ መንፈሰ ጸጋ ዘላዕሌከ ፡፡ ወብሂሎቱሰ ወለኢየሱስ ክርስቶስ ሰቀልዎ በሥጋሁ ምስለ ፍትወት ወኃጢአት፡፡ ምንት ውእቱ ፍትወት ዘእንበለ በሊዐ ዕፀ ዕልወት እንተ ገብርዎ አዳም ወሔዋን በፈቲወ ከዊነ አምላክ፡፡ወምንት ካዕበ ኃጢአት ዘእንበለ ኃጣውአ ደቂቆሙ እንተ ገብርዋ እም ፀአተ ገነት እስከ ስቅለተ ክርስቶስ፡፡ወበእንተዝ ጾረ ፍትወተ አዳም ወኃጣውአ ደቂቁ ወዐርገ ዲበ ዕፀ መስቀል፡፡ ገላ፫፥፲፫

፳፩ በከመ ያዕቆብ ገብረ ከልዔተ አምእስተ መሐስእ ውስተ መታክፍቲሁ ወለ ብሰ ልብሶ ለዔሳው ዘቦ ላዕሌሁ ጼና መዐዛ፡፡ ወአምእስተ መሐስእሰ ዘወደየ ውስተ መትከ ፍቱ በከመ ተኬነወት እሙ ከመ ይትመሰሎ ለዔሳው ሶበ ይገስሶ አቡሁ፡፡ ወከማሁ እግዚእነሂ ወደየ ኃጣውአ ዓለም ውስተ መትከፍቱ ወዐርገ ዲበ ዕፀ መስቀል ወአውዓያ በሕማማተ ሥጋሁ አሜሃ ውዕየ ሦክ ኀጢአት ዘበቈለ ውስተ ሥጋ አዳም አመ ረገሞ እግዚአ ብሔር እንዘ ይብል ሦክ ወአሜከላ ይብቍልከ ፡፡በከመ አልቦቱ ጸጕረ ለያዕቆብ አልቦቱ ኃጢአት ለኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ወበከመ ወደየ ያዕቆብ አምእስተ መሐስእ ዲበ መትከፍቱ ወከማሁ ጾረ ወልደ እግዚአብሔር ኃጣውአ ዓለም እንተ ኢኮነት እንቲአሁ፡፡ወበከመ ለብ ሰ ያዕቆብ ልብሰ ዔሳው ዘቦ ጼና መዐዛ ከማሁ ለብሰ እግዚእነ መዐዛ ጽድቆሙ ለቅዱሳን በዘያዜክሮ ለእግዚአብሔር አፈወ መዐዛ ነቢ ያት በዘያስተሠሪ ኃጣውኢሆሙ፡፡ ዘፍ፳፯፥፲፭

፳፪ በከመ አቅረበ ያዕቆብ ለአቡሁ መብልዐ ዘከመ ይፈቅድ ወከማሁ አቅረበ ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕተ ርእሱ ለወላዲሁ ቍርባነ ውኩፈ ሠናይ፡፡በከመ ይቤሎ አቡሁ ለያዕቆብ ኩና እግዚአ ለአኀዊከ ወከማሁ ክርስቶስ ኒ ኮኖሙ ርእሰ ለሐዋርያት፡፡ ወበከመ ወረደ ያዕቆብ ምድረ ሶርያ በብሒታዊ ከመ ይንግእ አዋልደ ላባ እኁወ እሙ ወበዐሥቱ ኮነ ከልዔ ተዓይነ ወከማሁ ወረደ እግዚእነ ውስተ ሲኦል

፳ ጳውሎስም ኢየሱስ ክርስቶስንም ከመሻትና ከኃጢአት ጋር በሥጋው ሰቀሉት አለ፡፡ ይህ የሐዋርያው ቃል ምድር ነው በጌታ ኢየሱስ መሻት አለን በክርስቶስ ዘንድ ኃጢአት አለን፡፡ ጳውሎስ አባቴ ሆይ ይህን የቃልህን ምሥጢር ተርጉምልኝ አልያም በአንተ ላይ ያደረ የጸጋ መንፈስ ይረዳኝ ዘንድ ባርከኝ፡ ኢየሱስ ክርስቶስንም ከመሻትና ከኃጢአት ጋር በሥጋው ሰቀሉት ማለቱስ አዳ ምና ሔዋን አምላክ ለመሆን በመሻት ካደረጉት የመተላለፍን ዛፍ ፍሬ ከመብላት በቀር መሻት ምንድር ነው ኃጢአትስ ሁለተኛ ከገነት ከመ ውጣት ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መስቀል ድረስ ያደረጉአቸው የልጆቻቸው ኃጢአት ካልሆነች በቀር ምንድር ናት ስለዚህም ነገር የአዳምን መሻት የልጆቹንም ኃጢአት ተሸክሞ ወደ ዕፀ መስቀል ወጣ፡፡ ገላ፫፥፲፫

፳፩ ያዕቆብ የሁለት ጠቦቶች ለምድ በትከሻዎቹ አድርጎ የዱር መዓዛ ያለበትን የዔሳውን ልብስ እንደለበሰ፡፡ በትከሻው ጫል ያደረገው የጠቦቶች ለምድ አባቱ በዳሰ ሰው ጊዜ ዔሳውን እንዲመስለው እናቱ እንደ ተጠበበች እንዲሁ ጌታችንም የዓለምን ኃጢአት በትከሻው ተሸክሞ ወደ ዕፀ መስቀል ወጣ የሥ ጋውም መከራዎች አቃጠላት ያን ጊዜ እግዚ አብሔር እሾህና አሜከላ ይብቀልብህ ብሎ በረገመው ጊዜ በአዳም ሥጋ የበቀለ የኃጢአት እሾህ ተቃጠለ፡፡ ያዕቆብ ጠጉር እንዳልነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት የለበትም፡፡ ያዕቆብ የጠቦቶች ለምድ በትከሻው እንደተሸከመ እንዲሁ የእግዚአብሔር ልጅ የእርሱ ያልሆነችይቱን የዓለምን ኃጢአት ተሸከመ፡፡ ያዕቆብ የዱር መዓዛ ያለውን የዔሳውን ልብስ እንደለበሰ እን ዲሁ ጌታችንም ኃጢአታቸውን ይቅር በሚ ልበት ገንዘብ የነቢያትን ባለመዓዛ ሽቱ ለአብ ያስብ ዘንድ የቅዱሳንን የጽድቃቸውን መዓዛ ለበሰ፡፡ ዘፍ፳፯፥፲፭

፳፪ ያዕቆብ ለአባቱ እንደሚወደው ምግብ እንዳቀረበ እንዲሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ የሠመረ ቁርባንና ያማረ መዓዛን ለወላጁ አቀረበ፡ ያዕቆብን አባቱ ለወንድምህ ጌታው ሁነው ብሎ እንደመረቀው እንዲሁ ክርስቶስም ለሐዋርያት ራስ ሆናቸው ያዕቆብ የእናቱን ወንድም የላባን ሴት ልጆች ሊያጭ ብቻውን ሆኖ ወደ ሶርያ ምድር እንደ ወረደ ሊመለስም የሁለት ክፍል ሠራዊት እን ደሆነ እንዲሁ ጌታችን የእናቱ ወገኖች

www.ethiopianorthodox.org

ባሕቲቱ ከመ የሐውጾሙ ለአበው ዘውእቶሙ
ነገደ ሕዝባ ለእሙ ወበፀአቱሰ ኮነ ክልዔ ተዓ
ይነ፡፡አሐዱ ኅብረ እምአዳም እስከ ሙሴ እለ
ነበሩ በተግሣጸ አበው ዘእንበለ ታስተርኢ ኦሪ
ት ሙሴ፡አሐዱ ኅብረ እምኦሪት ሙሴ እስከ
ስቅለተ ክርስቶስ እለ ነበሩ በሥርዓተ አይሁ
ድ እንዘ ይትቀነዩ ለትእዛዘ ኦሪት እንተ ተጽ
ሕፈት በጽላተ ሰማይ፡፡ለምንትኬ ወረዱ ውስ
ተ ሲኦል አበው ቀደምት እምአዳም እስከ
ሙሴ፡፡እስመ ረገሞ እግዚአብሔር ለአዳም
እንዘ ይብል እስመ ሰማዕከ ቃለ ብእሲትከ
ወበላዕከ እምነ ዕፅ ዘአነ ከላእኩከ ርግምተ
ትኩን ምድር በተግባርከ ሦክ ወአሜከላ
ይብቁ ልከ፡፡ተረግመት ምድር በኃጣውኢሁ
ለአዳም እስመ እምኔሃ ተወልደ፡፡ዝሰ
ይትሜሰል በመርገመ ይሁዳ ዘዐርገ ላዕለ
እሙ፡፡ እስመ ይቤ በመዝሙር ወትዘከር
ኃጢአተ አቡሁ በቅድመ እግዚአብሔር
ወኢይደመሰስ ጌጋያ ለእሙ፡፡

፳፫ ኢተስዕረ መርገማ ለምድር ዘኮነ
በእንተ ኃጢአተ አዳም ዘእንበለ በክዕወተ ደ
መ አምላክ፡፡ዘተወልደ እምወለተ አዳም በዘ
አሕመማ ጥዕየት ወበዘረገማ ግዕዘት፡፡ለምን
ትኬ ወረዱ ውስተ ሲኦል ነቢያት እግዚአብ
ሔር እለ ተቀንዩ ለሕገ ኦሪት እምአመ ሙሴ
ዘሰቀሎ ለአርዌ ምድር በገዳም እስከ አመ
ክርስቶስ ዘተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል፡፡እስመ
ይቤ ሙሴ በመጽሐፈ ሕግ ርጉመ ለይኩን
ኲሉ ብእሲ ዘኢይቀውም ይግበር ቃለ ዘው
ስተ ዝ ሕግ ወይብሉ ሕዝብ አሜን ወአ
ሜን፡፡

፳፬ ወበእንተዝ አልቦ ዘክህለ ጸዲቀ
በሕገ ኦሪት እስመ ኢፈጸሙ ገቢሮቶ፡፡ ወበ
እንተዝ ይቤ ጳውሎስ እስመ ዘገዖ መጽሐፍ
ለኲሉ ውስተ ኃጢአት፡፡ለእለ በኃጢአተ አዳ
ም ተኰነኑ ወአውዓየ ሦከ ኃጣውኢሆሙ ወአ
ሜከላ እከየ ምግባሮሙ በሕማማተ ሥጋሁ፡፡
ወለእለኒ ሰእኑ ጸዲቀ በሕገ ኦሪተ ሙሴ እስ
መ ኢፈጸሙ፡ወተዐደወ ትእዛዘ ዘለሊሁ ተመ
ጠወ እስመ አዘዘ እግዚአብሔር ከመ ኢይ
ንሥኡ ደቂቀ እስራኤል አዋልደ አሕዛብ
ወአዋልዲሆሙኒ ኢየሀቡ ለደቂቀ ነኪራን
ሕዝብ ከመ ኢያትልዋሆሙ ድኅረ አማልክተ
አበዊሆን፡፡ወበዝ ኃጢአት ስሀተ ሰሎሞን ወልደ
ዳዊት ወነሥአ እምነ ኵሉ አዋልደ ነገሥተ
አሕዛብ እስከ አትለዋሁ ድኅረ አማልክተ
አበዊሆን፡፡ወለሙሴሰ ኢተረክበ በላዕሌሁ

የሆኑትን አባቶች ይጉበኛቸው ዘንድ ብቻውን
ወደ ሲኦል ወረደ፡ ሲመለስም ሁለት ክፍል
ሠራዊት ሆነ አንዱ ከአዳም እስከ ሙሴ
የሙሴ ኦሪት ሳትሰጥ በአባቶች ተግሣጽ
የኖሩትን ያጠቃልላል፡ አንዱም በሰማይ ጽላት
ለተጻፈች ለኦሪት ትእዛዝ እየተገዙ ከሙሴ
ኦሪት መሰጠት እስከ ክርስቶስ መሰቀል ድረስ
በአይሁድ ሥርዓት የኖሩትን ያጠቃልላል፡፡ ከአ
ዳም እስከ ሙሴ የነበሩ የቀደሙ አባቶች
ለምን ወደ ሲኦል ወረዱ እግዚአብሐር አዳም
የሚስትህን ቃል ሰምተህ እኔ ከከለከልሁህ ዛፍ
በልተሀልና ከሥራህ የተነሣ ምድር የተረገመች
ትሁን እሾህና አሜከላም ይብቀልብህ ብሎ
ረግሞታልና ነው፡፡ ከእርሷ ተወልዷልና በአዳም
ኃጢአት ምክንያት ምድር ተረገመች፡፡ ይህስ
በእናቱ ላይ የደረሰውን የይሁዳን ርግማን
ይመስላል፡ ነቢይ በመዝሙር የአባቱ ኃጢአት
በእግዚአብሐር ፊት ትታሰብ የእናቱም በደል
አይፋቅ አለ፡፡

፳፫ ያለአምላክ ደም መፍሰስ በአዳም
ኃጢአት ምክንያት የመጣ የምድር ርግማን
አልተሻረም ከአዳም ሴት ልጅ የተወለደ እርሱ
ከፈረደባት መከራ ዳነች ከረገማት ርግማን ነፃ
ወጣች ዳግመኛም እባብን በምድረ በዳ ከሰቀለው
ከሙሴ ጊዜ ጀምሮ በዕፀመስቀል ላይ
እስከተሰቀለው እስከ ክርስቶስ ጊዜ ድረስ ለኦሪት
ሕግ የተገዙ የእግዚአብሔር ነቢያት ስለምን ወደ
ሲኦል ወረዱ፡ ሙሴ በሕግ መጽሐፍ በዚህ ሕግ
ውስጥ የተጻፈውን ቃል ይፈጽም ዘንድ የማ
ይጸና ሰው ሁሉ የተረገመ ይሁን ብሏልና
ሕዝቡም አሜን፡ አሜን ብለዋልና፡፡

፳፬ ስለዚህም ሕጉን መሥራትን ስላልፈጸሙ
በኦሪት ሕግ መጽደቅ የተቻለው የለም፡፡
ጳውሎስም ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ሁሉን ወደ
ኃጢአት ጨምሮታልና አለ፡፡ በአዳም ኃጢአት
የተፈረደባቸውን ማድረጓን ስላልፈጸሙ በሙሴ
ኦሪት ሕግ መጽደቅ ስተሳናቸውም የኃጢ አታቸ
ውን እሾህ የሥራቸውንም ክፋት አሜከላ
በሥጋው መከራዎች አቃጠለ፡፡ሙሴም ኢትዮጵ
ያዊቷን ሴት አገባ እርሱ ራሱ የተቀበለ ውን
ትእዛዝ ተላለፈ የእስራኤል ልጆች የአሕዛ ብን
ሴት ልጆች እንዳያገቡ ከአባቶቻቸው ጣዖታት
ኋላ እንዳያስከትሉአቸው የአሕዛብን ሴት ልጆች
እንዳያገቡ ሴቶች ልጆቻቸውንም ለተለዩ ሕዝብ
ልጆች እንዳሰጡ ታዘዋልና፡፡ በዚህም ኃጢአት
የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ተሳሳተ ከአባቶቻቸው
ጣዖታት ኋላ እስኪያስከትሉት ድረስ ከአሕዛብ
ነገሥታት ሴቶች ልጆች ሁሉ አገባ ሙሴ ግን
ኢትዮጵያዊቷን ሴት ከማግባት በቀር ጣዖታትን

www.ethiopianorthodox.org

አምልኮ ጣዖት ዘእንበለ ነሢአ ብእሲት ኢትዮጵያዊት ወበእንተዝ ኢኮነት ፍጽምተ ኃጢአቱ ከመ ኃጢአተ ሰሎሞን፡፡ ዘኁ፲፪÷፩ ፩ነገ ፲፩÷፬

፳፩ ወአሮንሂ ሊቀ ካህናት ገብረ ሰብኮ ዘላህም ወይቤ ናሁ አማልክቲከ እስራኤል፡፡ናሁኬ ለአሮን ወለሰሎሞን ጸንዓት ኃጢአቶሙ እምኃጢአተ ሙሴ በከመ ይቤ ዮሐንስ ሐዋርያ እስመ ቦ አበሳ ዘለሞት ወኢኮነ በእንቲአሃ ዘእብል ከመ ይስአሉ እስመ ኲሉ አበሳ ኃጢአት ይእቲ፡፡ወባሕቱ ቦ ጌጋይ ዘለ ሞት፡፡ ነአምር ከመ ኲሉ ዘተወልደ እም እግዚአብሔር ኢይኤብስ አላ ዘተወልደ እምነ እግዚ አብሔር የዐቅብ ርእሶ ወእኩይኒ ኢይስ ኀጦ፡፡ናሁኬ ዜነወ ወንጌላዊ ከመ ቦ አበሳ ዘኢኮነ ዘለሞት ወአዘዘ በእንቲአሁ ከመ ይጸ ልዩ፡፡ወእምድኅረዝ ይቤ ወቦ አበሳ ዘለ ሞት ወአኮ በእንቲአሃ ዘእብል፡፡ ናሁኬ መሀረ ኢጸ ልዮ በእንተ አበሳ ዘለሞት፡፡ምንት ሙሴኒ ብእሲተ ኢትዮጵያዊተ ነሥአ ውእቱ አበሳ ዘለሞት ዘእንበለ አምልኮ ጣዖት፡፡ወበእንተዝ ይቤ በተፍጻሜተ መልእክቱ ተዐቀቡ እምነ አማልክት፡፡

፳፪ ወበእንተዝ ትቤ ቅድስት ኦሪት ርጉመ ለይኩን ብእሲ ዘይገብር ግልፎ ወስብኮ ዘርኩስ በኀበ እግዚአብሔር፡፡ ወዳዊትኒ አበሰ በብእሲተ ኦርዮ ወዲበ ዝኒ ወሰከ አበሳ እንተ ተዐቢ ወፈነዎ ምስለ መጽሐፈ መልእክት እንተ ታቀ ትሎ ኀበ ኢዮአብ መልአከ ኃይሉ ወሞተ በኲናተ ፀር፡፡ወበዝ ተምዐ እግዚአብሔር ገቢሮታ፡፡ዐቢየ መዓተ ላዕለ ዳዊት በአፈ ነቢይ እንዘ ይብል አንተሰኬ ገበርኮኬ ለዝንቱ ነገርኬ በኀ ቡእኬ፡፡ወአንሰኬ እገብሮኬ በቅድመኬ ዝንቱኬ ፀሐ ይኬ ወበቅድመኬ ዝንቱኬ ሕዝብኬ፡፡ወይቤ ዳዊት አበስኩ ለእግዚአብሔር፡፡ወገሠጾ እግዚአብሔር ለዳዊት ወአኅዘኖ ህየተ ሞተ ኦርዮ ኬጥያዊ በሞ ተ ወልዱ ዘይልህቅ እምሰሎሞን እንተ ወለደት ሎቱ ቤርሳቤሕ፡፡ወካዕበሙ ገሠጾ እግዚአብሔር በማዕሌተ አቤሴሎም ወልዱ ዘሰደዶ እምጽርኃ መንግሥቱ ወተከለ ደብተራሁ በዲበ ናሕስ ወቦአ ኀበ ዐሥሩ አንስትያ አቡሁ፡፡ወእምዝ ሜጠ እግዚአብሔር ለዳዊት ውስተ ቤተ መንግሥቱ እምድኅረ ሞተ አቤሴ ሎም ወልዱ፡፡ ወአልቦ ዘይትረከብ እምነቢያት ፩ሂ ዘአልቦ ላዕሌሁ ምክንያተ ኃጣውእ፡፡ወበእንተዝ ተሠጥሙ ኲሎ ሙ ውስተ መርገመ ኦሪት፡፡ እስመ ትቤ ርጉመ ለይኩን ዘኢይፌጽም ገቢሮቶ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ፡፡ ፪ሳሙ፲፩÷፩ ፳፩ ፤፲፪÷፲፯

ማምለክ አልተገኘበትም ስለዚህም ኃጢአቱ እንደ ሰሎሞን ኃጢአት የጸናች ሆና አልተገኘችም፡፡ ዘኁ፲፪÷፩ ፩ነገ ፲፩÷፬

፳፩ ሊቀካህናቱ አሮንም የጥጃ ምስል ሠርቶ እስራኤል ሆይ እነሆ አምላኮችህ አለ፡፡ እነሆ የአሮንና የሰሎሞን ኃጢአት ከሙሴ ኃጢአት ይልቅ የጸናች ሆኘች ሐዋርያው ዮሐንስ እንደተናገረው ለሞት የሚያደርስ በደል አለ፡ ስለርሷ የምናገረው እንዲለምኑ አይደለም በደል ሁሉ ኃጢአት ናትና ዳሩ ግን ለሞት የሚያደረስ በደል አለ ከእግዚአብሔር የተወለደ ራሱን ይጠብቃል እንጂ ከእግዚአብሔር የተ ወለደ ሁሉ እንደማይበድል እናውቃለን ክፉ ውንም ነገር አያስተውልም እነሆ ወንጌላዊ ለሞት የሚያደርስ አበሳ እንዳለ ተናገረ ስለ ርሱም ይጸልዩ ዘንድ አዘዘ፡፡ ከዚህም በኋላ ለሞት የሚያደረስ በደል አለ ስለርሷ የምናገር አይደለም አለ፡፡ እነሆ ለሞት ስለሚያደርስ በደል አለመጸለይን አስተማረ ጣዖትን ከማምለክ በቀር ለሞት የሚያደረስ በደል ምንድር ነው ስለዚህም በመልእክቱ መጨረሻ ከአማልክት ተጠበቁ አለ፡፡ ፩ ዮሐ፭÷፲፮-፲፰

፳፪ ስለዚህም ነገር የከበረች ኦሪት በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ የሆነውን ጣዖትና ምስል የሚሠራ ሰው የተረገመ ይሁን አለች፡፡ ዳዊትም በኦሪዮ ሚስት በደለ በዚህም ላይ የም ትበልጠዋን በደል ጨመረ፡ የምታስገድ ለውን ደብዳቤ አሲዞ ወደ ጦሩ አለቃ ወደ ኢዮአብ ላከው በጠላት ጦርም ተወግቶ ሞተ በዚህም እግዚአብሔር በነቢይ አንደበት ይህን ነገር አንተ በሥውር ሠርተሸዋል እኔ ግን በዚህ ፀሐይ ፊት በዚህም ሕዝብ ፊት አደርገዋለሁ ብሎ በዳዊት ላይ ታላቅ ቁጣ ተቆጣ፡፡ ዳዊትም እግዚአብሔርን በድያለሁ አለ እግዚአብሔርም ዳዊትን ገሠጸው ስለ ኬጥያዊው ስለኦርዮም ሞት ብድራት ከሰሎሞን በሚበልጥ ቤርሳቤሕ በወለደችለት ልጁ ሞት አሳዘነው፡፡ ዳግመኛም ከመንግሥቱ አዳራሽ አስወጥቶ ባሳደደው ድን ኳኑንም በሰገነት ላይ ሠርቶ ወደ አሥሩ የአ ባቱ ዕቁባቶች በገባ በልጁ በአቤሴሎም በደ ል ገሠጸው፡፡ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ልጁ አቤሴሎም ከሞተ በኋላ ዳዊትን ወደ ቤተ መንግሥቱ መለሰው የኃጢአትን ምክንያት በርሱ ላይ የሌለበት ከነቢያት አንድ እንኳ አይገኝም ስለዚህም ሁላቸው በኦሪት ርግማን ውስጥ ሰጠሙ በዚህ የሕግ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን ማድረጉን የማይፈጽም የተረገመ ይሁን ትላለችና፡፡ ፪ሳሙ፲፩÷፩ ፳፩ ፤፲፪÷፲፯

www.ethiopianorthodox.org

፳፰ ለእለ ሀለው ውስተ ሲኦል ጸረ ኃጣውኢሆሙ ዲበ መትከፍቱ በከመይቤ ዮሐ ንስ መጥምቅ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘይጸውር ኃጣውአ ዓለም፡፡ኢሳይያስኒ ይቤ ውእቱ ነሥአ ደዌነ ወጸረ ሕማመነ፡፡ጳውሎስኒ ይቤ ዘከመዝኬ ይደልወነ ሊቀ ካህናት ዘይክል ሐሚመ ሕማመነ፡፡ወበዘአሕመምዎ ከሀለ ረዲኦቶሙ ለሕሙማን:: ወካዕበ ይቤ ጳውሎስ ወበከመ ጽኑሕ ለሰብእ መዊት ወእምድኅሬሁ ደይን፡፡ወከማሁ ክርስቶስ ምዕረ ሦዐ ርእሶ ከመ ይኅድግ ኃጢአቶሙ ለብዙኃን፡፡

፳፱ ስማዕ ኦ አብድ ዘከመ ይቤ ፊልፊለ ጥበብ ጳውሎስ፡፡ወበከመ ጽሑፍ ለሰብእ ምዕረ መዊተ አቅደመ ዘንተ በእንተ ፍልጠተ ነፍስ እምሥጋ፡፡አትለወ ወይቤ ወድኅሬሁ ደይን፡፡ናሁኬ አመረከ ርደተ ነፍሳተ አበው ውስተ ሲኦል፡፡ወእምዝ አትለወ በእንተ ፀአቶሙ እምሲኦል ወይቤ ወከማሁ ክርስቶስኒ ምዕረ ሦዐ ርእሶ ከመ ይኅድግ ኃጢአቶሙ ለብዙኃን፡፡ወበዝኒ አዮቀ ከመ ተኅድገ ኃጣውኢሆሙ ለአበው ቀደምት በሕማማተ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ እምቅድመ ይፍጥሮ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው፡፡ወተከለ ገነተ ለማኅደሩ ወሤመ ፀሐየ ውስተ ጠፈረ ሰማይ ከመ ያብርህ ሎቱ፡፡ወአስተባረየ ወርኅ ወከዋክብተ በኑኃ ለያልይ በዘይትፌሣሕ በሰርጐ ሰማያት ሶበ ያንቀዐዱ፡፡ በከመ ያርእይዎ ለሕፃን ሰርጐ ዘይዔድዋ ለአዕይንቲሁ፡፡

፴ ወአመ ፈጠሮሂ ኢኅደጎ በጠባይዒሁ ከመ ጠባይዐ እንስሳ ወአዕዋፍ አላ ነፍሐ ውስተ ገጹ መንፈሰ ሕይወት ወረሰዮ ልብወ በኀልዮ ወነባቤ በሞገሰ ቃል፡፡ ወአልቦ ዘተረከበ ዜና ውስተ ገጸ መጽሐፍ ዘከመ ነፍሐ እግዚአብሔር ውስተ ገጸሙ መንፈሰ ሕይወት ኢዲበ መላእክት ቅዳሴ ወኢዲበ መላእክተ ገጽ እስመ ተፈጥሩ በንባበ አፉሁ ሶበ ይቤ በመዝሙር ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እምሰማያት፡ ይሴብሕዎ በአርያም ፡ይሴብሕዎ ፀሐይ ወወርኅ፡ ይሴብሕዎ ኵሉ ኃይሉ፡ ይሴብሕዎ ከዋክብት ወብርሃን፡ ይሴብሕዎ ሰማያት ፡ወማይኒ ዘመልዕልተ ሰማያት ይሴብሑ ለስመ እግዚአብሔር፡ እስመ ውእቱ ይቤ ወኮኑ፡፡ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ፡ ወአቀሞሙ ለዓለም ዓለም፡ ትእዛዘ ወሀቦሙ ወኢኀለፉ፡፡ ወካዕበመ ይቤ ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ፡ ወለእለ ይትለአክዎ

፳፰ መጥምቁ ዮሐንስ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚሸከም የእግዚአብሔር በግ እንዳለ በሲኦል ለነበሩት ኃጢአታቸውን በት ከሻው ተሸከመ፡፡ ኢሳይያስም እርሱ ደዌአችን ተቀበለ መከራችንንም ተሸከመ አለ፡፡ ጳውሎስም ሕመማችንን መታመም የሚችል እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት በመከራ ያስፈልገናል መከራ ባጸኑበትም ገንዘብ ያሉትን ሊረዳቸው ተቻለው አለ፡፡ ሁለተኛም ጳውሎስ መሞት ከርሱም በኋላ የፈርድ ቦታ ለሰው የተጠበቀ እንደሆነ እንዲሁ ክርስቶስ የብዙዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ሲል ራሱን አንድ ጊዜ ሠዋ አለ፡፡ ኢሳ፶፫፥፬ ዮሐ፩፥፳፱ ዕብ፪፥፳፰

፳፱ አንተ ሰነፍ የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ የተናገረውን ስማ ሞት ለሰው ፈጽሞ የተጠበቀ እንደሆነ አለ ይህን ነፍስ ከሥጋ መለየት አስቀደመ አስከትሎም ከእርሱም በኋላ ደይን አለ እነሆ የአባቶችን ነፍሶች ወደ ሲኦል መውረድ አመለከተህ፡፡ ከዚያም አያይዞ ከሲኦል ስለ መውጣታቸው እንዲሁ ክርስቶስም የብዙዎችን ኃጢአት ይቅር ይል ዘንድ ራሱን አንድ ጊዜ ሠዋ አለ፡፡ በዚህም ሳይፈጥረው አስቀድሞ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ወድዶታልና በኢየሱስ ክርስቶስ መከራዎች የቀደሙ አባቶች ኃጢአት ይቅር እንደተባለ አስታወቀ፡፡ ለማደሪያው ገነትን ተከለ ያበራለትም ዘንድ በሰማይ ጠፈር ፀሐይን ሾመለት ለሕፃን ለዓይኖቹ የሚያምረውን ጌጥ እንደሚያሳዩት ወደላይ አቅንቶ ባየ ጊዜ በሰማያት ጌጥ ደስ ይለኝ ዘንድ በሌሊት ርዝማኔ ጨረቃንና ከዋክብትን አፈራረቀለት፡፡

፴ በፈጠረውም ጊዜ እንደ እንስሳና አዕዋፍ ባሕርይ ባሕርዩን አልተወውም በፊቱ ላይ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት በማሰብ የሚያስተውልና ሞገስ ባለውም ቃል የሚናገር አደረገው እግዚአብሔር በምስጋና መላእክትም ላይ በመላእክተ ገጽም ላይ በፊታቸው የሕይወትን እስትንፋስ እፍ እንዳለባቸው በመጽሐፍ ክፍል ተጽፎ የተገኘ ዜና የለም ነቢይ በመዝሙር እግዚአብሔርን በሰማያት አመስግኑ በአርያም ያመስግኑታል መላእክቱም ሁላቸው ያመስግኑታል ሠራዊቱ ሁሉ ያመስግኑታል ፀሐይና ጨረቃ ያመስግኑታል ከዋክብትና ብርሃን ያመስግኑታል ሰማያት ያመስግኑታል ከጠፈር በላይ ያለ ውኃም የእግዚአብሔርን ስም ያመስግናል እርሱ ተናግሯልና ሆኑ እርሱም አዝዟልና ተፈጠሩ ለዘላለምም አጸናቸው ትእዛዝን ሰጣቸው ትእዛዙንም አልተላለፉም እንዳለ ይሁኑ ይፈጠሩ ባለ ጊዜ በአንደበቱ ንግግር ተፈጥረዋልና ዳግመኛም መላእክቱን መንፈስ የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ነደ እሳት፡፡ መዝ፻፫÷፫፤፻፵፰÷፯

፴፭ ወበእንተ አዳምሰ ትብል ቅድስት ኦሪት ወገብሮ ግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው እምነ መሬት ምድር ወነፍሐ ውስተ ገጹ መንፈሰ ሕይወት፡፡ወኮነ እጓለ እመሕያው በመንፈሰ ሕይወት ውትከለ እግዚአብሔር አምላክ ውስተ ኤዶም ገነተ ቅድመ መንገለ ጽባሕ ወሤሞ ሀየ ለእጓለ እመሕያው ዘገብረ ፡፡እግዚአ ብሔርሰ ፈጠሮ ሕያወ ለአዳም ወውእቱ አጥረየ ሞተ በዐማፃሁ፡፡እግዚአብሔርሰ ሤሞ ንጉሠ ዲበ ኵሉ ፍጡራን በከመ ትቤ ቅድስት ኦሪት፡፡ወአምጽኦሙ ኀበ አዳም ከመ ይርአይ ወምንተ ይሰምዮሙ፡፡ወሰመዮሙ አዳም ለለነፍሰ ሕይወት ውእቱ ይከውን ስሞሙ ፡፡ዳዊትኒ ይቤ ወሤምኮ ዲበ ኵሉ ግብረ እደዊከ፡፡ወኵሎ አግረርከ ሎቱ ታሕተ እገሪ ሁ፡፡አባግዐኒ ወኵሎ አልህምተ፡፡ወዓዲ እንስሳ ዘገዳም፡፡አዕዋፈ ሰማይኒ ወዓሣተ ባሕር ወዘኒ የሐውር ውስተ ፍኖተ ባሕር፡፡ ዘፍ፪÷፯-፱ ፤፲፱ መዝ፲÷፫

፴፮ ወበእንተዝ ይቤ ዳዊት ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ::ዝሰ ይተረጐም ኢያእ መረ አዳም ዕበየ ዘላዕሌሁ እንዘ ሀሎ ውስተ ገነተ ተድላ ወእንዘ ይትኤዘዙ ሎቱ ኵሉ ፍጥ ረት፡፡ሰምዐ ምክረ ጸላዒሁ ወበልዐ እምዕፀ ዕልወት በፈቲወ ከዊነ አምላክ፡፡ ወእምዝ አት ለወ ወይቤ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ፡፡ምንት ውእቱ ተመስሎ እንስሳ ዘእንበለ ተከሥቶ ዕርቃኑ ማእከለ ዕፀዊሃ ለገነት ሶበ ነፍጸ አጽፈ ብርሃን ዘላዕሌሁ ኀደገ አጽፈ ብርሃን ሶበ ተዐደወ ትእዛዘ እግዚአ ብሔር ወኢኃደጎ ልቡናሁ ዘመንፈሰ ሕይወት፡፡ኀፈረ በእንተ ተከሥቶ ዕርቃኑ ወገብሩ ሎሙ መዋርዕተ እምቈጽለ በለስ ውእ ቱኒ ወብእሲቱኒ:: መዝ፵፰÷፲፪

፴፯ ወእምድኅረዝ ይቤ ቃለ መዝሙር ወለሊሃ ፍናቶሙ ዕቅፍቶሙ::ምንት ውእቱ ዕቅፍቶሙ ለአዳም ወለሔዋን ዘእንበለ ፍናተ ኃጢአት እንተ ገብርዋ በአፀደ መቅደሱ ለእግ ዚአብሔር፡፡ተዐቅፈት ሔዋ በቃለ ከይሲ ወተ ዓቅፈ አዳም በቃለ ሔዋ ብእሲቱ ወእምዝ ወጽኡ እምገነተ ተድላ:: ወእምድኅረ ወጽኡ እምገነት ተሠይሙ ዐቀብት እምኪሩቤል ወሱ ራ ፌል ከመ ይዕቀቡ አናቅጺሃ ለገነት በኵናተ እሳት ዘያንበለብል ከመ ኢይትመየጡ አዳም ወሔ ዋን ኀበ ማኅደሪሆሙ:: ዘፍ፫÷፳፬

ያደርጋቸው የሚያገለግሉትንም እሳት አለ:: መዝ፻፫÷፫፤፻፵፰÷፯

፴፭ ስለ አዳም ግን የከበረች ኦሪት እግዚአብሔርም የሰውን ልጅ ከምድር አፈር አበጀው በፊቱም ላይ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት አለች:: የሰው ልጅ በሕይወት እስትንፋስ ተፈጠረ እግዚአብሔር አምላክም በፀ ሐይ መውጫ በኩል በኤዶም ገነትን ተከለ በዚህያም ያበጀውን የሰውን ልጅ አኖረው፡ እግዚ አብሔር አዳምን ሕያው አድርጎ ፈጠረው እርሱ ግን በዐመፃው ሞትን ገዛ::እግዚአብሔ ርስ በፍጡራን ሁሉ ላይ ሾመው የከበረች ኦሪት በምን ስም እንደሚጠራቸው ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው አዳምም የሕይወት ነፍስ ላላቸው ሁሉ በስማቸው እንደጠራቸው ስማ ቸው ያው ሆነ እንዳለች፡ ዳዊትም በእጆችህ ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁለንም ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት በጎችንና ላሞችን ሁሉ ከእን ግደገናም የዱር እንስሳትንና የሰማይ ወፎችን የባሕር ዓሦችንና በባሕር ወስጥ በፍጡራን ሁሉ ላይ ንጉሥ አድርጎ ሾመው:: ዘፍ፪÷፯-፱ ፤፲፱ መዝ፲÷፫

፴፮ ስለዚህም ዳዊት ሰው ግን ክቡር ሲሆን አላወቀም አለ::ይህስ አዳም በተድላ ገነት ሳለ ፍጥረትም ሁሉ ሲታዘዙለት ሳለ በእርሱ ያለውን ክብር አላወቀም የጠላቱንም ምክር ሰምቶ አምላክነትን በመሻት ከመተላለፍ ዛፍ ፍሬ በላ ከዚህም አስከትሎ ልብ እንደሌላቸው እንደ እንሰሳ ሆነ መሰላቸውም አለ:: በእርሱ ላይ የነበረ የብርሃን መጐናጸፊያ በተገፈፈ ጊዜ በገነት ዛፎች መካከል ራቁትነቱ ከመገለጡ በቀር እንሰሳትን መምሰል ምንድር ነው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተላለፈ ጊዜ የብርሃን ግምጃ ተለየው የሕይወት መንፈስ ያለበት ልቡናው ግን አልተለየውም ዕርቃኑ በመገለጡ አፈረ እርሱም ሚስቱም ከበለስ ቅጠ ል ግልድም ለራሳቸው አደረጉ:: መዝ፵፰÷፲፪

፴፯ ከዚህም በኋላ የመዝሙሩ ቃል ጐዳናቸው ራሷ እንቅፋታቸው ሆነች አለ በእግዚአብሔር በመቅደሱ አፀድ ከሠሩአት የኃጢአት መንገድ በቀር የአዳምና የሔዋን እንቅፋታቸው ምንድር ነው:: ሔዋን በእባብ ቃል ተሰናከለች አዳምም በሚስቱ በሔዋን ቃል ተሰናከለ ከዚህም በኋላ ከተድላ ገነት ወጡ፡ ከገነት ከወጡ በኋላ አዳምና ሔዋን ወደ ቀደመ ማደሪያቸው እንዳይመለሱ በመንበገበግ የእሳት ሰይፍ የገነትን ደጃፎች ይጠብቁ ዘንድ ከኪሩ ቢልና ከሱራፌል ወገን ጠባቂዎች ተሾሙ:: ዘፍ፫÷፳፬

፴፬ በከመይቤሉ ኤርምያስ ወሕዝቅኤል አበው በልዑ ቆዐ ወደቂቆሙ ፀርሱ ስነኒ ሆሙ፡ጳውሎስኒ ይቤ እምአዳም እስከ ሙሴ ለእለሂ አበሱ ወለእለሂ ኢአበሱ ቀነዮሙ ሞት፡፡ወበእንተ ነቢያትኒ ይቤ ወእም እመ ሙሴ እስከ ክርስቶስ እለ ተጸምዱ ታሕተ ቅኔ ኦሪት እስመ ኢይጸድቅ ኲሉ ዘነፍስ በገ ቢረ ሕገገ ኦሪት፡በእንተ ምንትኬ እስመ መርገም ባቲ ለኢያጽድቆ ዘእንበለ ለዘፈጸመ ገቢሮታ፡፡ ሕዝ፲፰፥፪ ሮሜ፭፥፲፬

፴፭ ንትመየጥኬ እንከሰ ኀበ ቃለ መዝ ሙር ዘመትልወ ንበቱ ለዘይቤ ከመ አባግዕ ሞት ይርእዮሙ በሲኦል፡፡ ናሁኬ አብጽሐ ቃለ መዝሙር ኀበ ህላዌሆሙ ለነፍሳተ አዳ ም ወደቂቁ ዘከመ ይርዕዮሙ ሞት ውስተ ሲኦ ል፡፡ወእምድኅረዝ ይቤ ወይቀንይዎሙ ራት ዓን በጽባሕ፡እለ መኑ እሙንቱ ራትዓን ዘእን በለ ዓቀብተ ገሃነም እለ አልቦሙ አድልዎ ለገጽ ኢይምህኩ ንጉሠ በእንተ ዕበዩ ለእመ አበሰ ወኢያኄዕሩ ምስኪነ በእንተ ንዴቱ ለእመ ኢአበሰ፡፡ወዘይቤሰ ከመ አባግዕ ሞት ይርዕዮሙ በሲኦል ወይቀንይዎሙ ራትዓን በጽባሕ ይትረጐም ዘዮም ተውህበ ኃጥእን ለፍትሐ ሞት ወበጽባሕ ትትልዎሙ መቅ ሠፍተ ደይን እምኀበ ዓጸውተ ሲኦል፡፡

፴፮ ወእምድኅረዝ ይቤ ነቢይ ወባሕቱ እግዚአብሔር ያድኅና ለነፍስየ እምእደ ሲኦል ሶበ ይነሥኡኒ፡፡ተናገረ ነቢይ ዘከመ ያድኅና እግዚአብሔር በሕማማተ ወልዱ ዋሕድ፡፡ ወበርደተ ወልድ ዋሕድ ውስተ ቈላተ ደይን ኮነ ጸአቶሙ ለነፍሳተ ጻድቃን፡፡ወበእንተዝ ይቤ ነቢይ አኮ በተንባል ወአኮ በመልአክ አላ ለሊሁ ይመጽእ ወያድኅኖሙ፡፡ መዝ፵፰፥፲፭

፴፯ ወካዕበመ ይቤ በመዝሙር አንሣ እኩ አዕይንትየ መንገለ አድባር፡፡ እምአይቴ ይምጻእ ረድኤትየ፡፡አድባረ ይሰምዮሙ ለነቢ ያት ወኀሠሠ ረድኤተ እምኔሆሙ ወአልቦ ዘረከበ፡ ወእምዝ አእመረ በመንፈስ ትንቢት ከመ አልቦ ረድኤት ዘእንበለ በክርስቶስ:: ወበእንተዝ ይቤ ረድኤትየሰ እምኀበ እግዚአ ብሔር ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ኢሳይያስኒ ዜነ ወ ዘከመ ይወርድ ውስተ ሲኦል ወይቤ ወሖ ርኩ ኀበ ብእሲት ነቢይት ወፀንሰት ወወለደት

፴፬ ኤርምያስና ሕዝቅኤል አባቶች ጮርቃ በሉ ልጆቻቸውም ጥርሶቻቸውን ጨረሱ እንዳለ የኃጢአታቸውን ስሕተት በልጆቻቸውም ላይ ተቆጠረ፡ ጳውሉስም ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛ ቸው አለ፡ስለ ነቢያትም ከሙሴ ጊዜ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ በኦሪት አገዛዝ ሥር የተጠ መዱ የኦሪትን ሕግ በመሥራት ሥጋ ለባሽ ሁሉ አይጸድቅምና አለ፡፡ በምንድር ነው እርሷን ማድረግ ለፈጸመ ካልሆነ በቀር ላለመጽድቅ ርግማን አለባትና፡፡ ሕዝ፲፰፥፪ ሮሜ፭፥፲፬

፴፭ እንግዲህስ የትንቢቱ ተከታይ ወደ ሆነው እንደ በጎች ሞት በሲኦል ያሠማራቸዋል ወደሚለው የመዝሙር ቃል እንመለስ፡ እነሆ የመዝሙሩ ቃል ሞት በሲኦል እንዴ ሠማራቸው ወደ አዳምና ልጆቹ ነፍሶች አነዋወር አደረሰን ከዚህም በኋላ ቅኖች በነግህ ይገዙአቸዋል አለ፡፡ ፊት አይተው ከማያደሉ ከገሃነም በረኞች በቀር ቅኖች እነማን ናቸው ከበደለ ንጉሥን ስለ ክብሩ አይራሩለትም ካልበ ደለም ችግረኛውን ስለችግሩ አያስጨንቁትም ሞት እንደበጎች በሲኦል ያሠማራቸዋል፡፡ ቅኖች በነግህ ይገዙአቸዋል ያለው ግን በአሁኑ ጊዜ ለሞት ፍርድ በተሰጡ ኃጥአን ይተረጎማል በጠዋት የደይን መቅሠፍት ከሲኦል በረኞች ዘንድ ትከተላቸዋለች፡፡

፴፮ ከዚህም በኋላ ነቢዩ፡ ነገር ግን በወሰዱኝ ጊዜ እግዚአብሔር ነፍሴን ያድናታል አለ፡፡ ነቢዩ እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ መከራዎች እንደሚያድነው ተናገረ፡ በአንድ ልጁም ወደ እንጦርጦስ መውረድ የጻድቃን ነፍሶች መውጣት ሆነ ስለዚህም ነቢዩ በአማላጅ አይደለም በመልእክተኛም አይደለም ራሱ ይመጣል ያድናቸውማል አለ፡፡ መዝ፵፰፥፲፭

፴፯ ዳግመኛም በመዝሙር ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ አለ፡፡ ነቢያትን ተራሮች አላቸው ከእነርሱም ርዳ ታን ፈለገ ያገኘው ግን የለም ከዚህ በኋላ በትንቢት መንፈስ በክርስቶስ ካልሆነ በቀር ርድታ እንደሌለ ዐወቀ ስለዚህም መረዳቴስ ሰማይና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው አለ፡፡ ኢሳይያስም ወደ ሲኦል እንደሚወርድ ወደ ሴት ነቢይት ዘንድ ሄድሁ፡፡ ፀነሰች ወንድ ልጅም ወለደች እግዚአብሔርም ስሙን ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛም ቸኮለ ብለህ ጥራው አለኝ ብሎ

ወልደ፡፡ወይቤለኒ እግዚአብሔር ሰምዮ ሰሞ ፍጡነ ማኅርከ ወሩጽ ጌውው፡፡አይ ይእቲ ነቢይት ፅንሰት ዘወለደት ወልደ ዘእንበለ እግዝእትነ ማርያም ዘወለደቶ ለመድኃኒነ፡፡ወአይኑ ውእቱ ማህርካ ዘእንበለ ነፍሳተ አበው እለ ማህረኮሙ እምውስተ ሲኦል፡፡ ወአይኑ ካዕበ ጌዋ እለ ጌወወ መድኃኒነ ዘእንበለ ነፍሳተ ነቢያት እለ አውጽኦሙ እም አፀደ ደይን፡፡

፴፰ ዳዊትኒ ይቤ እትፌሣሕ ወእት ካፈል ምህርካ፡፡ከመ ዘሎቱ ይነግር ለወልደ እግዚአብሔር እስመ እምሥርወ ዳዊት ተሠገወ፡፡ወዘይቤሰ እትካፈል ምህርካ ነፍሳተ አበው ውእቱ በከመ ንቤ ቀዳሚ፡፡ወእምዝ አትለወ ወይቤ ወእሳፈር አዕጻዳተ ቈላት፡፡ ዘንተኒ ይብል በእንተ ቈላተ ደይን ከመ ዘቦ ርስተ እስመ ፈቀደ ይትመሰሎሙ ለአበዊሁ እመንገለ እሙ፡፡ ተአንገደ ኀበ እለ ይነብሩ ውስተ ቈላተ ደይን ወረደ ከመ ያውጽኦሙ ወአኮ ከመ ይግቀይ ምስሌሆሙ፡፡አርኀወ ሎሙ መናስግተ ሲኦል ከመ ይፃኡ አዳም ወደቂቁ ወሙሴ ምስለ ሕዘቢሁ፡ሠዐራ ለመርገመ ኦሪት እንተ አሥጠመቶሙ ውስተ ቀላየ ገሃነም፡፡ኦሪትሰ ቅድስት ይእቲ ወትእዛዛኒ ቅዱስ ወባሕቱ ከኖሙ ሕምዘ ኢፈጸሞታ፡፡ መዝ፶፱፥፮፣፻፰፥፩ ኢሳ፳፥፫

፴፱ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ አልቦ ዘክህለ ፈጽሞታ ለትእዛዘ ኦሪት ወከመ ኵሉ ተሠጥመ ውስተመርገማ ኀለየ ከመ አልቦ ዘይክል ፈቲሐ ማእሰሪሃ ዘእንበለ ውእቱ ባሕቲቱ ዘአንበረ ማእሰረ መርገም ውስቴታ፡፡ ወካዕበመ ሐለየ ከመ አልቦ ዘይክል አርኅዎታ ለአንቀጸ ገነት ዘእንበለ ውእቱ ባሕቲቱ ዘለሊሁ ዓፀወ፡፡ወበእንተዝ ተሰብአ እምወለተ አዳም ከመ ይሥዐር መርገሞ ለአዳም ተወልደ እምወለተ አይሁድ ከመ ይሥዐር መርገማ ለኦሪት፡፡ወአመ ሰሙን ተከስበ በከመ ሥርዓተ ዕብራውያን ከመ ይትዐወቅ በላዕ ሌሁ ትእምርተ አብርሃም፡፡ዐርገ ውስተ በዓለ መጸለቶሙ ከመ ያውፅኦሙ ለነቢያት እም ጽላሎተ ሞት፡ገበረ ፍሥሕ ምስለ አርዳኢሁ ከመ ይፈጽም ሥርዓተ ብሊተ ወከመ ያስተዳልዎሙ ለመሀይምናን ለሐዲስ ፋሲካ፡፡ ወበምሴተ ኀሙስ ጠብሐ በግዐ ፋሲካ ከመ ይፈጽም ሕገ ዘተሠርዐ በምድረ ግብጽ አመ ፀአቶሙ ለደቂቀ እስራኤል፡፡ወበሳኒታሁ ኮነ ለሊሁ በግዐ ፋሲካ ወተጠብሐ በእደ ሰቃልያን። በልዐ

ተናገረ አለኝ በሉ ተናገረ። መድኃኒታችንን ከወለደች ከእመቤታችን ከማርያም በቀር ይህቺ የፀነሰች ወንድ ልጅ የወለደች ሴት ነቢይት ማን ናት ከሲኦል ከማረካቸው ከአባቶች ነፍሶችስ በቀር ምርኮ የቱ ነው ዳግመኛም ከፍርድ ቦታ ካወጣቸው ከነቢያት ነፍሶች በቀር መድኃኒታችን የማረከው ምርኮ ምንድር ነው።

፴፰ ዳዊትም ደስ ይለኛል ምርኮም እካፈላለሁ አለ። እንደራሱ አድርጎ ለእግዚአብሔር ልጅ ተናገረ ከዳዊት ባሕርይ ሰው ሆኗልና ምርኮ እካፈላለሁ ያለው በፊት እንደተናገርን የአባቶች ነፍሶች ናቸው ከዚህም አስከትሎ በቀላዮች አፀዶች እሰፍራለሁ። አለ ይህንንም ርስት እንዳለው ሆኖ ስለ ፍርድ ቆላ ተናገረ።ከእናቱ ወገን አባቶቹን ሊመስላቸው ወድዷልና በፍርድ ቆላ በሚኖሩት ዘንድ እንግዳ ሆነ ያወጣቸው ዘንድ ወረደ ከእነርሱ ጋር ሊሠቃይስ አይደለም አዳምና ልጆቹ ሙሴም ከወገኖቹ ጋር ይወጡ ዘንድ የሲኦልን ቁልፎች ከፈተላቸው በገሃነምም ጥልቅ ውስጥ ያስመጠቻቸውን የኦሪትን ርግማን ሻራት ኦሪትስ የከበረች ናት ትእዛዟም የከበረ ነው ነገር ግን እርሷን አለ መፈጸማቸው መርዝ ሆነባቸው። መዝ፶፱፥፮ ፣፻፰፥፩ ኢሳ፳፥፫

፴፱ እግዚአብሔርም የኦሪትን ትእዛዝ ሊፈጽማት የተቻለው እንደሌለ ሁሉም በርግማኗ ውስጥ እንደተዘፈቀ ባየ ጊዜ በውስጧ የርግማን ማሠሪያ ካስቀመጠ ከእርሱ ብቻ በቀር ማሠሪያዋን መፍታት የሚችል እንደሌለ አሰበ። ዳግመኛም እርሱ የዘጋትን ከእርሱ ብቻ በቀር የገነትን ደጃፍ ሊከፍታት የሚችል እንደሌለ አሰበ፡ ስለዚህም የአዳምን ርግማን ይሽር ዘንድ ከአዳም ሴት ልጅ ሰው ሆነ የኦሪትን ርግማን ይሽር ዘንድ ከአይሁድ ሴት ልጅ ተወለደ በስምንተኛውም ቀን ለአብርሃም የተሰጠ ምስክር በእርሱ ላይ ይታወቅ ዘንድ እንደ ዕብራውያን ሥርዓት ተገረዘ። ነቢያትን ከሞት ጥላ ሊያወጣቸው ወደ ቂጣ በዓላቸው ወጣ ያረጀችውን ሥርዓት ሊፈጽም ምእመናንንም ለአዲስ ፋሲካ ሊያዘጋጃቸው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካ አደረገ። በኀሙስ ምሽት የእስራኤል ልጆች በወጡ ጊዜ በግብጽ ምድር የተሠራለቸውን ሕግ ይፈጽም ዘንድ የፋሲካ በግ አረደ። በመግሥቱም እርሱ ራሱ የፋሲካ በግ ሆነ በሰቃዮችም እጅ ታረደ በእርሾ ያልተለወሰውን የአይሁድ ቂጣ በላ።

www.ethiopianorthodox.org

ናእተ አይሁድ ዘኢተሎሰ በብሉእ፡፡ ወእም ድኅረ ድራር ወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ኅብስተ ሥጋሁ ናእተ ሐዲስ ዘነሥአ እምባሕቲታ ድንግል ዘኢተሎሰት በብሉእ ብእሲ ዘውእቱ ዘርአ ሙላድ፡፡ ዘፍ፲፯+፳፬ ማቴ፳፯+፳-፳፱ ገላ፬+፬

፴ ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ ወአንት ሙሰ ተቀደሱ ለሐዲስ ናእት፡፡ ለምንትኬ ኢወሀበ ሥጋሁ ወደሞ ኢእምቅድመዝ ወኢእምድኅረዝ አላ አመንተወ ምስለ በግዐ ፋሲካ ዘኦሪት፡፡በደመ በግዕ ዘመሥዋዕተ ፋሲካ ገብረ ላቲ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ለምኩራብ፡፡ ወበቍርባነ ሥጋሁ ወደሙ ኅጸያ ለቤተክርስቲያን፡፡ወባሕቱ ገብረ ፍልጠተ ማእከለ መሥዋዕተ ኦሪት ወማእከለ መሥዋዕተ ወንጌል በኃጊበ እገሪሆሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይገብር በአርአያ ጥምቀት እስመ ኢይደልዎ ለኢጥሙቅ ነሢአ ቍርባን፡፡ዮሐንስ አመ አጥመቆ አንበረ እዴሁ ዲበ ርእሱ፡፡ወእግዚእ ኢየሱስ አመ ሐፀቦሙ ለአርዳኢሁ መዝመዘ እገሪሆሙ በለንጽ ወአስተናጽሐ ርስሐተ ሰኳንዊሆሙ በእዴሁ ቅድስት፡፡ዮሐ፲፫+፭ ፩ቆር፭+፯

፴፩ ኀበ ዮሐንስ አስተርአየ ዕበየ ክህነት ወኀበ እግዚእ ኢየሱስኒ ትሕትና ተልእኮ እስመ ህላዌሃ ለርእሰ መልዕልተ ኵሉ ወህላዌሆን ለአእጋር መትሕተ ኵሉ፡ስምዐ ኮነ አብ በፈለገ ዮርዳኖስ እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ፡፡ዝ ስምዓ ጽድቅ አኮ በእንተ ዘአጥመቀ አላ በእንተ ዘተጠምቀ :ተሠጠ ሰማይ ወወረደ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ጸዓዳ ወነበረ ዲቤሁ አኮ ኀበ ዮሐንስ አላ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ፡፡ እም አመ ኀፀበ እግረ አርዳኢሁ በ፺ወ፫ ዕለት ወረደ መንፈስ ቅዱስ ከመ ዘእሳት አኮ ኀበ ዘኀፀበ አላ ኀበ ዘተኀጽቡ፡፡ ማቴ፫+፲፮ ሐዋ፪+፬

፴፪ በከመ ኢተፀርዐ ስብሐተ ህላዌሁ ለወልድ በጽርኃ አርያም እምዕለተ ትስብእቱ እስከ ዕለተ ዕርገቱ፡፡ወከማሁ ኢተጸርዐ ስብሐተ ህላዌሁ ለመንፈስቅዱስ በጽርኃ አርያም አመ ርደቱ ውስተ ጽርኃ ጽዮን ላዕለ ሐዋርያት፡፡ አምላክነሰ በህየ ሥሉስ ወበዝየ ኢፍሉጥ፡፡በህየ ምሉእ ወበዝየ እኩት በአፈ ፬ ወንጌላውያን፡፡ በህየ ኃይል ዘኢያስተርኢ ወበዝየ እሳት ዘኢይትለከፍ፡፡ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ

ከኦሪትም በኋላ የመዋለጃ ዘር በሚሆን በወንድ እርሾ ካልተለወሰች ከብቻዋ ከድንግል የነሣውን አዲስ ቂጣ የሥጋውን ኅብስት አድርጎ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው፡፡ ዘፍ፲፯+፳፬ ማቴ፳፯+፳-፳፱ ገላ፬+፬

፴ ስለዚህም ነገር ጳውሎስ እናንተስ ለአዲስ ቂጣ ተቀደሱ አለ ስለምን ሥጋና ደሙን ከዚህ አስቀድሞ ከዚህም በኋላ አልሰጠም ከኦሪት ፋሲካ በግ ጋር መንታ አደረገ እንጂ በፋሲካ የመሥዋዕት በግ ደም የምኩራብን የፍቺዋን ደብዳቤ ሰጣት ለቤተክርስቲያንም የሥጋውን የደሙን ቍርባን አጨላት፡ ዳሩ ግን ያልተጠመቀ ቍርባኑን ሊቀበል አይገባውምና በጥምቀት ምሳሌ አድርጎ የደቀመዛሙርቱን እግር በማጠብ በኦሪት መሥዋዕትና በወንጌል መሥዋዕት መካከል ልዩነት አደረገ፡፡ ዮሐንስ ባጠመቀው ጊዜ እጁን በራሱ ላይ አኖረ ጌታ ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን ባጠባቸው ጊዜ እግሮቻቸውን በማበሻ ጨርቅ አሽ የተረከዛቸውንም እድፍ በቅድስት እጁ አነፃ፡፡ ዮሐ፲፫+፭ ፩ቆሮ፭+፯

፴፩ በዮሐንስ ዘንድ የክህነት ክብር ተገለጠ በጌታ ኢየሱስ ዘንድ ግን የማገል ገልትሕትህና ታየ፡ የራስ አኗኗሯ ከሁሉ በላይ ነውና የእግሮችም አኗኗ ሯቸው ከሁሉ በታች ነውና፡፡ አብ በዮር ዳኖስ ወንዝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት ብሎ መሰከረ ይህ የጽድቅ ምስክርነት ስለተጠማቂው እንጂ ስለ አጥማቂው አይደለም ሰማይ ተከፈተ መንፈስ ቅዱስም በነጭ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀመጠ በዮሐንስ ላይ አይደለም በጌታ ኢየሱስ ላይ እንጂ የደቀመዛሙርቱን እግር ካጠበበት ቀን ጀምሮ በሀምሣ ሦስተኛ ቀን መንፈስቅዱስ ወደ አጠበው ያይደለ ወደታጠቡት በእሳት አምሳል ወረደ፡፡ ማቴ፫+፲፮ ሐዋ፪+፬

፴፪ ሰው ከሆነባት ቀን ጀምሮ እስከ አረገበት ቀን ድረስ የወልድ የባሕርይ ምስጋና በጽርሐ አርያም እንዳልተጓደለ እንዲሁ የመንፈስቅዱስም የባሕርይ ምስጋና የባሕርይ ምስጋና በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ አልተቋረጠም፡፡ አምላካችንስ በዚያ በሦስትነት ያለ በዚህም ያልተለየ በዚያ ሙሉ በዚህም ጎጸጽ የሌለበት በዚያ በአራት እንስሳ እንደበት የተመሰገነ በዚህም በአራቱ ወንጌላውያን የተመሰገነ በዚያ የማይታይ ኃይል በዚህም የማይዳሰስ እሳት ነው፡፡ቅዱስ ቅዱስ

www.ethiopianorthodox.org

ሥሉስ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ፡፡ፀባ ዖት ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ አድባረ ወአውግረ ባሕረ ወአፍላገ ወኵሎ አጽናፈ ኀበ ዘኢያስተርኢ ወኀበ ያስተርኢ ቅድሳተ ስብሐቲሁ፡፡

፺፫ ከመዝ ትትሜሃር ወከመዝ ትሜህር እምነ ወእምከሙ ቅድስት ቤተክርቲያን እንተ ይእቲ ንጽሕት ርግብ ክነፊሃ በብ ሩር ዘግቡር ወገበዋቲሃኒ በሐመልማለ ወርቅ እንተትጸውር ወንጌለ መለኮት ወትትመረጐዝ በዕፀመስቀል ወትብሎሙ ለእለ ይፀመድዋ ዝ ውእቱ አክሊ ለ ሃይማኖትየ ዘበአስማተ ሥላሴ ተጸፈረ፡፡ዝ ውእቱ ጌራ መድኃኒትየ ዘአወፈዩኒ ሐዋርያ ት፡፡ዝ ውእቱ አጽፈ ጥምቀትየ ዘአጥረይክዋ በፈለገ ዮርዳኖስ፡፡

ቅዱስ ሦስት አብና ወልድ መንፈስቅዱስ አቻናፊ ፍጹም በሰማያትና በምድር በተራሮችና በኮረብቶች በባሕርና በወንዞች በዳርቻዎችም ሁሉ በማይታየውና በሚታየው ሁሉ ላይ በቅድ ስናው ምስጋናው መልቶ የሚኖር ነው፡፡

፺፫ ክንፎቿ በብር ጉኖቿም በወ ርቅ ሐመልማል የተለበጡ የመለኮትን ወንጌል የምትሸከም በዕፀመስቀልም የምትመረኮዝ ንጽ ህት ርግብ የሆነች እናታችን የእናንተም እናታ ችሁ ቅድስት ቤተክርስቲያን እንዲህ ተማረች እንዲህም ታስተምራለች የሚያገለግሉአትንም በሥላሴ ስም የተጐነጐነ የሃይማኖቴ አክሊል ይህ ነው ሐዋርያት የሰጡኝ የድኅነቴ ዘውድ ይህ ነው ከዮርዳኖስ ወንዝ የገዛሁት የጥምቀቴ ግምጃ ይህ ነው ትላቸዋለች፡፡

፺፬ ወእምዝ ንትመየጥ ኀበ ዜና ነገር ዘከመ ቦአ ወልድ ዋሕድ ኀበ መርገመ ኦሪት እንዘ ኢኮነ ርጉመ በኢፈጸሞ ሕገጊሃ ከመ ነቢያት እለ ኃየሎሙ ሕግ ዘሥጋ ውእቱሰ ወኢተዐደወ ወኢምንትኒ እም ትእዛዘ ሙሴ በከመ ይቤሎ ለዘለምጽ ለሊሁ አንጽሖ ሑር አፍትን ርእሰከ ለካህን ወአብእ መባእከ በእ ንተ ዘንጻሕከ በከመ አዘዘ ሙሴ ከመ ይኩን ስምዐ ላዕሌሆሙ፡፡ወአልቦ እንከ ዘአግመራ ለዐቂበ ትእዛዘ ኦሪት ዘእንበለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንጹሕ እምኃጢአት ዘወሀበ ኦሪት ለሙሴ በመለኮቱ ወተቀንየ ለትእዛዘ ኦሪት በትስ ብእቱ፡፡ወባሕቱ ቀርበ ውስተ ጕንደ መስቀል ከመ ይስዐር መርገማ እስመ ትቤ ቅድስት ኦሪት ወለእመቦ ዘአበሰ ለእመ በጽሐ ጌጋዩ ከመ ይኩነን መዊተ ትሰቅልዎ ዲበ ዕፅ ወትቀትልዎ ወኢይቢት ሥጋሁ ዲበ ዕፅ አላ ቀቢረ ትቀብርዎ በይእቲ ዕለት እስመ ርጉም ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ዘስቁል ዲበ ዕፅ፡፡ቦአ ውስተ መርገማ በተሰቅሎ ወአኮ በአ ብሶ፡፡ወበእንተዝ ተፈትሐ ኵሉ ማእሠረ መ ርገማ፡፡ወበከመ ይቤ ጳውሎስ ተሣየጠነ ዘኃ ጢአት ወኮነና ለይእቲ ኃጢአት በሥጋሁ፡፡ ዘዳ፳፩፥፳፫ ማቴ፲፥፬ ገላ፫፥፲፫

፺፬ እንግዲህስ አንድ ወልድ የሥጋ ሕግ እንዳቸነፋቸው እንደ ነቢያት ሕግጋቷን ባለመፈጸም የተረገመ ሳይሆን ወደ ኦሪት ርግማን እንደገባ ወደ ሚነገርበት ዜና ነገር እንመለስ እርሱ ግን ለምጽ የነበረበትን ሰው ከለምጹ ካነጻው በኋላ ሂድ ራስህን ለካህን አስመርምር ምስክርም ሊሆንባቸው ሙሴ እንዳዘዘው ስለመንጻትህ መባዕ አቅርብ እንዳለው ከሙሴ ትእዛዝ ምንም ምን አልተላለፈም፡፡ እንግዲህ ከኃጢአት ንጹህ ከሆነ በመለኮቱም ለሙሴ ኦሪትን ከሰጠው በሰውነቱም ስለኦሪት ትአዛዝ ከታዘዘው ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር የኦሪትን ትእዛዝ ለመጠበቅ የቻላት የለም፡፡ ዳሩ ግን ርግማኗን ይሽር ዘንድ ወደ መስቀል ግንድ ቀረበ፡፡ የከበረች ኦሪት የበደለ ቢኖር በደሉም ሞት ይፈረድበት ዘንድ የሚያደርሰው ከሆነ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ ግደሉት በድኑ ግን በእንጨት ላይ አይደር በዚያች ቀን መቅበርን ቅበሩት እንጂ በዕንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ብላለችና፡፡ በመበደል ያይደለ በመሰቀል ወደ ርግማኗ ገባ ስለዚህም ነገር የርግማኗ ማሠሪያ ሁሉ ተፈታ፡፡ ጳውሎስም እንደተናገረ ክርስቶስ ከኦሪት ርግማን ዋጀን ዳግመኛም ኃጢአትን ማድረግን የማያውቅ ኃጢአት የሚስማማውን ሥጋ ለበሰ፡፡ በዚያችም ኃጢአት በሥጋ ፈረደባት አለ፡፡ ዘዳ፳፩፥፳፫ ማቴ፲፥፬ ገላ፫፥፲፫

፺፭ ክርስቶስ እመርገማ ለኦሪት፡፡ ወካዕበሙ ይቤ ዘኢየአምር ኃጢአት ለብሰ ሥጋ በከመ ለብሰ ሥጋ ዘኃጢአት እም ወለ ቶሙ ለኃጥአን እንተ ይእቲ ንጽሕት በሥጋሃ ወቅድስት በነፍሳ ወኢለከፈ ኃጣውአ አቡሃ ለወልዳ ወከማሁ ቦአ ውስተ መርገመ ኦሪት ወኢበ

፺፭ በሥጋዋ የነጻች በነፍሷም የተቀደሰች ከሆነች ከኃጢአተኞች ሴት ልጅ ኃጢአት የሚስማማውን ሥጋ እንደለበሰ የአባቶ ቿም ኃጢአት ልጇን እንዳላገኘው እንዲሁ ወደ ኦሪት ርግማን ገባ ርግማኗ ግን አልደረሰበትም፡፡ ዳሩ ግን ማሠሪያዎች ሁሉ ተፈቱ ሐዋርያት መድኅን ኦሪትና ነቢያትን ሊያፈርሳቸው አልመ

www.ethiopianorthodox.org

ጽሑ መርገማ ወባሕቱ ተፈትሐ ኲሉ ማዕሠሪሃ፡፡በከመ ይቤሉ ሐዋርያት እስመ እመጽአ መድኅን ይንሥቶሙ ለኦሪት ወለነቢያት አላ ከመ ይፈጽሞሙ ወከመ ይፍታኅ ማእሰረ ዘውስተ ዳግም ሕግ፡፡ቀደመ ፈቲኖ ማእሰሪሆሙ ለሙቁሐን እንዘ ሀሎ ዲበ ዕፀ መስቀል እስመ ኢይክሉ ሙቁሐን አንሶስዎ በእግሪሆሙ እንዘ እሱራን እማንቱ፡፡

፵፮ ወእምድኅረ ፀአተ ነፍሱ ወረደ ውስተ ሲኦል ከመ ያውጽኦሙ እምዓጸደ ሙስና በከመ ይቤ ሐዋርያ፡፡ወሖረ ኀበ እለ ሙቁሕታ ትነብር ነፍሶሙ፡፡ ወሰበከ ሎሙ ለእለ ክህድዎ ቀዲሙ፡፡ወካዕበመ ይቤሉ ሐዋርያት በመጽሐፈ ቅዳሴ ዘአኰቴተ ቍርባን ሰፍሐ እደዊሁ ለሕማም ከመ ሕሙማነ ይፍታሕ ወማእሰረ ሰይጣን ይብትክ ወይኪድ ሲኦለ ቅዱሳነ ይምራሕ ሥርዓተ ይትክል ወትንሣኤሁ ያውቅ፡፡አቅደሙ ብሂለ ሰፍሐ እደዊሁ ለሕማም በእንተ ሰፍሐተ እዴሁ ዲበ ዕፀ መስቀል ከመ ይፍታሕ በሕማሙ ሕማማቲሆሙ ለእለ ውስተ ደይን፡፡ወእምዝ አትለው ወይቤሉ ማእሰረ ሰይጣን ይብትክ ምንት ውእቱ ማእሰሪሁ ለሰይጣን ዘእንበለ ገቢረ ኃጢአት ዘነበረ ኀበ አበው፡፡ወይኪድ ሲኦለ ምንት ውእቱ ኪደታ ለሲኦል እስመ ዘአንሶሰወ ውስተ ገነት ፍና ሰርክ ከመ ያውጽኦሙ ለአዳም ወለሔዋን አመ ሔሶሙ በእንተ በሊዓ ዕፅ፡፡ ከማሁ አንሶሰወ ውስተ አዕጻዳተ ደይን በሰርከ ዓርብ ዘአመ ሕማሙ ወቤዘዎሙ ለአዳም ወለሔዋ ወለኲሎሙ ነቢያተ እስራኤል በሞቱ ማሕየዊ፡፡ወዓዲ ቦ ስምዓ ጽድቅ እምቃለ ኪዳን ዘይቤ ዘተውህበ ለሙስና ዘትካት ብእሴ አድኅንከ በመስቀሉ ለዋሕድከ ወሐደስኮ በዘኢይማስን፡፡

፵፯ ወካዕበመ ቦ ስምዓ ጽድቅ እም ቃለ ኪዳን በእንተ ርደቱ ውስተ ሲኦል ይቤ እምድኅረ ሐመ ወረደ ውስተ ሲኦል ዘውእቱ ነፍሳተ ሙታን ጌወዎ ለሕይወት ወአብኦሙ ውስተ ገነት ትፍሥሕት ምስለ አዳም አቡሆሙ ወምስለ ሔዋ እሞሙ ወምስለ ነፍስ ፈያታይ ዘተመሰጠ እምዲበ መስቀል፡፡ሰሰሉ ዐቀብተ አናቅጺሃ ለገነት።

፵፰ ናሁ አብጻሕነ ለክሙ ስምዐ ከመ ነበሩ ነቢያት ውስተ ሲኦል ወዘከመሂ አውጽኦሙ እግዚእነ በሞቱ ወአብኦሙ ውስተ ገነት ትፍሥሕት፡፡ወበ እንተሰ ዘነበሩ አበው ቅዱሳን ውስተ ዓጸደ ደይን ንንግር አኮ በተጽዕሮ ከመ ኃጥአን አላ ]ናኅይ እንዘ ተዐቅቦሙ ጠለ ምሕረቱ ለእግዚ

ጣምና ሊፈጽማቸው በዳግም ሕግ የተጻፈውንም ማሠሪያ ይፈታ ዘንድ ነው እንጂ እንዳሉ፡ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ የእሥረኞችን ማሠሪያ መፍታትን አስቀደመ እሥረኞች ታሥረው ሳለ በእግሮቻቸው መመላለስ አይችሉምና፡፡

፵፮ ነፍሱ ከወጣች በኋላ ሐዋርያው ታሥራ ወደ ምትኖር ነፋሳቸው ሄደ እንዳለ፡ ከጥፋት አጸድ ያወጣቸው ዘንድ ወደ ሲኦል ወረደ ቀደሞ ለካዱትም ሰበከላቸው ዳግመኛም ሐዋርያት የቊርባንን ምስጋና በሚናር በቅዳሴ መጽሐፍ ሕሙማንን ይፈታ ዘንድ የሰይጣንንም እሽክላ ይበጣጥስ ዘንድ ሲኦልንም ሊረግጥ ቅዱስንንም ሊመራ ሥርዓትን ይትክል ዘንድ መነሣቱንም ያስታውቅ ዘንድ እጆቹን ለሕመም ዘረጋ እንዳሉ፡፡ በሕመሙ በሲኦል ያሉትን ሕመማቸውን ይፈታ ዘንድ ስለእጅ በዕፀ መስቀል ላይ እጆቹን ለሕመም ዘረጋ ማለትን አስቀደሙ ከዚህም አስከትለው የሰይጣንን እሽክላ ይበጣጥስ ዘንድ አሉ፡፡ በአባቶች ዘንድ ከነበረ ኃጢአትን ከማድረግ በቀር የሰይጣንን ማሠሪያው ምንድው ነው ሲኦልን ሊረግጥ አለ፡ የሲኦል መረገጧ እንዴት ነው፡ በለስን በመብላት ምክንያት ሲነቅፋቸው አዳምና ሔዋንን ያስወጣቸው ዘንድ በሠርክ ጊዜ በገነት ውስጥ እንደ ተመላለሰ እንዲሁ በመከራው ሰዓት በዓርብ ምሽት በሲኦል አፀዶች ተመላለሰ፡፡ አዳምና ሔዋንን የእስራኤልንም ነቢያት ሁላቸው ሕይወትን በሚሰጥ ሞቱ ተቤዣቸው፡፡ ዳግመኛም በኪዳን ምስጋና ለጥፋት የተሰጠ የቀደመውን ሰው በአንድያ ልጅህ መስቀል አዳንህ በማይጠፋም ገንዘብ አደስኸው የሚል የእውነት ምስክር አለ፡፡

፵፯ ዳግመኛም በኪዳን ምስጋና ወደ ሲኦል ስለመውረዱ መከራን ከተቀበለ በኋላ ወደ ሲኦል ወርዶ የእርሱ የሆኑትን የሞቱ ሰዎች ነፍሳት ወደ ሕይወት ማረከ ከአባታቸው ከአዳም ከእናታቸውም ከሔዋን ጋር ከመስቀልም ላይ ከተነጠቀ ከሽፍታው ነፍስ ጋር ደስታ ወዳለበት ገነት አስገባቸው የገነት ደጃፎችን የሚጠብቁትም ተወገዱ፡፡

፵፰ እነሆ ነቢያት በሲኦል እንደኖሩ ጌታችንም በሞቱ አውጥቶ ደስታ ወደ ሚገኝበት ገነት እንዳስገባቸው ምስክር አቀረብንላችሁ በሲኦል አፀድ ስለ ኖሩ አባቶች ግን እንናገር፡፡ እንደ ኃጥአን በመጨነቅ አይደለም ሦስቱን

አብሔር በከመ ዐቀቦሙ ለ፫ ደቂቅ ማእከለ እቶነ እሳት ዘባቢሎን፡፡ወበከመ ዐቀቦ ለዮናስ በከርሠ ዐንበሪ፡፡ወበከመ ዐቀቦ ለዳንኤል በውስተ ግበ አናብስት ርኁባን፡፡ኢያድኅኖሙ እግዚአብሔር ለአናንያ ወአዛርያ ወሚ ሳኤል እምእደ ናቡከ ደነጾር ንጉሥ አላ አድ ኅኖሙ እም ነበልባለ እሳት መፍርህ እምድ ኅረ ወረውዎሙ ውስቴቱ፡፡

፵፱ ሶበሰ አድኃኖሙ እመዐተ ንጉሥ እምቅድመ ይባኡ ማእከለ እቶነ እሳት ዘይ ጥሕር ፍልሐቱ ከመ ነጐድጓደ ክረምት እመ ኢተሰብሐ ኃይለ አድኅኖቱ ለእግዚአብሔር ወእመ ኢገነየ ሎሙ ንጉሥ፡፡ወሶበ ርእዮሙ ጥዑያነ ማእከለ እቶን ወፍሡሐነ በማእከለ ነበልባል ገነየ ለእግዚአብሔር ወአንከረ በእንተ ሥኑ ለራብዕ ወይቤ ገጹ ለራብዕ ወልደ እግዚአብሔር ይመስል ዘኢያስተርአየ በአቱ ውስተ እቶን አስተርአየ ነሶሳው ማእከለ እቶን ምስለ ሠለስቱ ደቂቅ እለ ተከለሉ በሞገሰ ሥላሴ፡፡ወበእንተዝ አእመረ ንጉሥ ከመ እግዚአ እሳት ውእቱ አምላከ ፫ ደቂቅ ወአዘዘ ይዑድ ዓዋዲ እንዘ ይብል ኵሉ ዘኢሰገደ ለአምላከ ሲድራቅ ወሚሳቅ ወአብደናጎ ሞተ ለይሙት፡፡ ዳንጅ፥፩-፴

፶ ወበእንተ ዮናስኒ ንንግር ኢያድኅኖ እግዚ አብሔር እምተሠጥሞ ውስተ ባሕር አላ ዐቀቦ በከርሠ አንበሪ ከመ ኢያ ኅዝዞ ሞገደ ባሕር፡፡ሶበሰ ድኅነ በከርሠ ሐመር እም ኢተሰብሐ ኃይለ አድኅኖቱ ለእግዚ አብሔር ወበአሕማርሰ ልማድ ውእቱ ቦ ዘይ ድኅን ወቦ ዘይትኀጐል፡፡ወበከረሠ ዐንበሪሰ ኢልማድ ውእቱ ዑቃቤ ዘእንበለ ሙሳኔ፡፡ ከርሠ ዐንበሪ ኮኖ ለዮናስ በከመ ከርሠ ዝህር ዘጎልጎታ፡፡ በከመ ቦአ በድነ እግዚእ ኢየሱስ ውስተ ከርሠ መቃብር እንዘ ሕያው ውእቱ መለኮቱ ከማሁ ኮነ በአተ ዮናስ ውስተ ከርሠ ዐንበሪ እንዘ ሕያው ውእቱ ወይትሐሰብ ከመ ዘሞተ በኀበ እለ ወረውዎ፡፡

፶፩ ወበእንተዝ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ትእምርተ ተኃሥሥ ዛቲ ትውልድ ወትእምርትሰ ኢይትወሀባ ዘእንበለ ትእም ርተ ዮናስ ነቢይ፡፡ወበከመ ዮናስ ነበረ ውስተ ከርሠ ዐንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ከማሁ ይሄሉ ወልደ እጓለ እመሕያው ውስተ ከርሠ ምድር ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ

ብላቴኖች በባቢሎን የእሳት እቶን መካከል ዮናስንም በዓሣ ዐንባሪ ሆድ ዳንኤልንም በተራቡ አንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንደጠበቀችው የእግዚአብሔር የምሕረት ጠል እየጠበቅቻቸው በዕረፍት ኖሩ እንጂ እግዚአብሔር አናንያንና አዛርያን ሚሳኤልንም ከንጉሥ ናቡከደነጾር እጅ አላዳናቸውም በውስጡ ከጣሉአቸው በኋላ ከሚያስፈራው የእሳት ነበልባል አዳናቸው እንጂ፡፡

፵፱ ፍላቱ እንደ ክረምት ነጐድጓድ ወደ ሚጮህ የእሳት ዕቶን መካከል ሳይገቡ አስቀድሞ ከንጉሥ ቁጣ አድኗቸውስ ቢሆን የእግዚአብሔር የማዳኑ ኃይል ባልተመሰገነ ንጉሥም ባልተንበረከከላቸው ነበር፡፡ በዕቶኑ መካከል ጤነኞች በነበልባልም መካከል ደስተኞች ሆነው ባያቸው ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገደ ስለ አራተኛውም ማማር የአራተኛውም መልኩ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል ብሎ አደነቀ ወደ ዕቶን መግባቱ ያልታየ በሥላሴ ሞገስ በተጠበቁ ከሦስቱ ብላቴኖች ጋር በዕቶኑ መካከል መመላለሱ ታየ፡፡ ስለዚህም ንጉሥ የሦስቱ ብላቴኖች አምላክ የእሳት ጌታ እንደሆነ ዐወቀ አዋጅ ነጋሪም ለሲድራቅና ለሚሳቅ ለአብደናጎም አምላክ ያልሰገደ ሁሉ ሞትን ይሙት ብሎ አዋጅ እንዲነግር አዘዘ፡፡ ዳንጅ፥፩-፴

፶ ስለዮናስም እንናገር እግዚአብሔር ወደ ባሕር ከመጣል አላዳነውም የባሕሩ ሞገድ ወደታች እንዳያሰርገው በዓሣ ዐንበሪ ሆድ ውስጥ ጠበቀው እንጂ ፡፡በመርከብ ውስጥ ሆኖ ድኖ ቢሆን የእግዚአብሔር የማዳኑ ኃይል ባልተመሰገነ ነበር፡፡ በመርከቦችማ የተለመደ ነው የሚድን አለ የሚጠፋም አለ በዓሣ ዐንባሪ ሆድ ውስጥ ግን ከመጥፋት በቀር መጠበቅ ያልተለመደ ነው፡፡ የዓሣ ዐንበሪ ሆድ ለዮናስ እንደ ጎልጎታ መቃብር ሆነው፡፡ መለኮቱ ሕያው ሲሆን የጌታችን ኢየሱስ በድን መቃበር ውስጥ እንደገባ በሕይወት ያለ ሲሆን የዮናስ ወደ ዓሣ ዐንበሪ ሆድ መግባት እንዲሁ ሆነ በወረወሩት ዘንድ ግን እንደ ሞተ ሰው ተቆጠረ፡፡

፶፩ ስለዚህም ነገር ጌታችን በወንጌል ይህች ትውልድ ምልክት ትሻለች ምልክትስ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር አይሰጣትም ዮናስ በዓሣ ዐንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደቆየ እንዲሁ የሰው ልጅም በምድር ልብ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል ብሎ ተናገረ፡፡ ዮናስ በመርከብ ውስጥ ድኖ ቢሆን ከእግዚአብሔር ፊት ይሸሻግ ዘንድ ወደ

www.ethiopianorthodox.org

ለያልየ፡፡ሶበሰ ድኅነ ዮናስ በከርሠ ሐመር እምሐረ ሀገረ ተርሴሰ ከመ ይትኅጣእ እምገጸ እግዚአብሔር፡፡ወበእንተዝ አወፈዮ እግዚአብሔር ለልጐተ ባሕር ወልጐተ ባሕር አወፈየቶ ለከርሠ ዐንበሪ፡፡ዐንበሪሰ ውኅጦ በከመ ልማድ ወእግዚአብሔር ዐቀቦ እሙስና፡ ወሖረ ዐንበሪ በትእዛዘ እግዚአብሔር ሠሉሰ መዋዕለ መሠሉሰ ለያልየ ወአብጽሖ ሀገረ ነነዌ ወቄየ፡፡ ወሶበርእያ ዮናስ ለሀገር ገነየ ለእግዚአብሔር ወአእመረ ከመ ንጉሥ ውእቱ ዲበ ማያት ወሥልጣኑኒ ህልው ውስተ ቀላይ፡፡ ዮና፩÷፩-፲፯፡፪÷፲፩ ማቴ፲፪÷፴፱

ተርሴስ አገር በሄደ ነበር ስለዚህም እግዚአብሔር ለጥልቅ ባሕር አሳለፎ ሰጠው ጥልቅ ባሕርም ለዓሣ ዐንበሪ ሆድ ሰጠችው ዓሣ ዐንበሪውም እንደለመደው ዋጠው እግዚአብሔር ግን ከጥፋት ጠበቀው ዓሣ ዐንበሪውም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ተጓዞ ወደ ነነዌም ሀገር አድርሶ ተፋው ዮናስም አገሪቱን ባየ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገደ በውኆች ላይ እርሱ ንጉሥ እንደሆነ ሥልጣኑም በውቅያኖስ ላይ እንዳለ ዐወቀ፡፡ ዮና፩÷፩-፲፯ ፥፪÷፲፩ ማቴ፲፪÷፴፱

፺፪ ወበእንተ ዳንኤልኒ ንንግር ከመ ኢያድኅኖ እግዚአብሔር እምውዴቶሙ ለሰብአ ሜዶን ወፋርስ ወእምዳርዮስ ንጉሥ ፡፡ ወባሕቱ አድኅኖ እምአፈ አናብስት ርኁባን እንዘ ኅትምት ግብ ላዕሌሆሙ ኢሰሐጥዎ በአስናኒሆሙ ወኢነከይዎ በአፅፋሪሆሙ አላ ነበሩ ምስሌሁ ጽውማኒሆሙ፡፡ሶበሰ አድኅኖ እግዚአብሔር እም ውዴተ ሜዶን ወፋርስ ወእም እደ ዳርዮስ ንጉሦሙ እምኢተሰብሐ ኃይለ አድኅኖቱ ለእግዚአብሔር፡፡እስመ ብዙኃን እለ ይድኅኑ እምውዴተ ቢጾሙ ወእመዓተ ንጉሥ እመሂ በፍትሐ ኰነኔሆሙ ወእመሂ በተስናን ቃሎሙ፡፡ወነቢረ ስንእሰ ምስለ አናብስት ውስተ ፩ ግብ አኮ ለኵሉ ዘይደልዎ ዘእንበለ ዳእሙ ከመ ዳንኤል ዘኮነ ሕይወቶሙ በአምልኮ እግዚአብሔር ጤቀላ ወእለ ለአናብስት እንዘ ስጉዳን ታሕተ እገሪሁ ለነቢይ ወአንከረ ንጉሥ ወአእመረ ከመ እግዚአ አናብስት ውእቱ አምላከ ዳንኤል፡፡ወአዘዘ ከመ ይደይዎሙ ምስሌሃ ሰማዕት፡፡ ሶበ አዘዘ ንጉሥ ከመ ውስተ ውእቱ ግብ ለመስተዋድያን ቀነጹ አናብስት እማዕምቀ ግብ ወቀለጽዎሙ ዘእንበለ ይብጽሑ ውስተ ምድር፡፡ዳን፮÷፩-፳፯

፺፪ ስለዳንኤልም እግዚአብሔር ከሜዶንና ከፋርስ ሰዎች ክስ ከንጉሥ ዳርዮስም እጅ እንዳላዳነው እንናገራለን ነገር ግን ከተራቡ አንበሶች አፍ አዳነው ጉድጓድ በእነርሱ ላይ የተዘጋች ስትሆን በጥርሶቻቸው አልነከሱትም በጥፍሮቻቸውም አልቧጩሩትም ተርበው ከእርሱ ጋር ተቀመጡ እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ከሜዶንና ከፋርስ ሰዎች ክስ ከንጉሥ ዳርዮስም እጅ አድኖትስ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሐር የማዳኑ ኃይል ባልተመሰገነ ነበር፡፡ በዳኝነታቸው ፍርድም ቢሆን በቃላቸውም ክርክር ቢሆን ከባልንጀራቸው ከንጉሥም ቁጣ የሚድኑ ብዙዎች አሉና፡፡ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ከአንበሶች ጋር ተስማምቶ መቀመጥ ግን እንደ ዳንኤል ሕይወታቸውን እግዘአብሔርን በማምለክ እንደጸና እንደ ጤቀላና ከእርሷም ጋር እንደነበሩ ሰማዕታት ነው እንጂ፡፡ ለሁሉ የሚሆንለት አይደለም ንጉሥ የጉድጓዱን ማኅተም እንዲገልጡ ባዘዘ ጊዜ አንበሶቹን በነቢዩ እግሮች በታች ሰግደው አገኛቸው ንጉሥም አደነቀ፡፡ የዳንኤልም አምላክ የአንበሶች ጌታ እንደሆነ ዐወቀ ከሳሾቹንም ወደ ምድር ሳይደርሱ አንበሶቹ ከጉድጓድ ውስጥ ዘልለው ዋጡአቸው፡፡ ዳን፮÷፩-፳፯

፺፫ እቶነ ባቢሎን ለእለ ውስተ ውሳጢታ ዓቀበቶሙ ዘእንበለ ሙስና ወለዘእንተ አፍኣሰ አውዐየቶሙ እምርኁቅ፡፡አናብስተ ዳርዮስ ንጉሥ ነበሩ ስንእ ውስተ ግብ ምስለ ነቢይ ዘወሀብዎሙ ከመ ይብልዕዎ ወእመል ዕልተ ግብ መሠጥዎሙ ለመስተዋድያኒሁ ፡፡አማንኬ ዘይቤ ነቢይ ጻድቅሰ እማዕገተ ያመስጥ ወቤዛ ዚአሁ ይትዋሀብ ኃጥእ፡፡ በከመ ኢያውዐየቶሙ ነበልባለ እቶን ለሠለስቱ ደቂቅ ከማሁ ኢያውዐዮሙ ነበልባለ ሲኦል

፺፫ የባቢሎን ዕቶን በውስጧ የነበሩትን ያለጥፋት ጠበቀቻቸው በውጭ የነበሩትን ግን ከሩቅ አቃጠለቻቸው፡፡ የንጉሥ ዳርዮስ አንበሶች በጉድጓድ ውስጥ እንዲበሉት ከሰጡአቸው ከነቢዩ ጋር በስምምነት ተቀመጡ ከሳሾቹን ግን ከጉድጓድ አፋፍ ላይ ተናጠቁአቸው፡፡ ነቢዩ ጻድቁ ግን ከወጥመድ ያመልጣል ያለው እውነት ነው የእርሱንም ፈንታ ኃጥእ ይቀበለዋል፡፡ የእቶኑ ነበልባል ሦስቱን ብላቴኖች እንደላቃጠላቸው እንደ ሲኦል ነበልባል ቅዱሳን አባቶችን አላቃጠላቸውም

www.ethiopianorthodox.org

ለአበው ቅዱሳን እስመ ጠለ ምሕረቱ ለእግዚ
አብሔር ዐቀበቶሙ፡፡በከመ ይቤ ነቢይ እስመ
ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ፡፡ በከመ
ኢያኀሰሙ አናብስት ላዕለ ዳንኤል እንዘ ህል
ዋን ምስሌሁ ውስተ ፩ ግብ ከማሁ ኢያሕ
ሠሙ ዐቀብተ ገሃነም ላዕለ ነቢያት ንጹሐን
እንዘ ህልዋን ምስሌሆሙ ውስተ ቀላየ
ደይን፡፡

፺፬ ወበእንተሰ ህላዌሆሙ ለነቢያት
ውስተ ሲኦል እስከ ምጽአተ ክርስቶስ ይከ
ሥቱ ማኅተመ ግብ ረከቦሙ ይቤ ዳዊት መኑ
ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት፡፡ ወመኑ
ዘያድኅና ለነፍሱ እምእደ ሲኦል፡፡ወበዝኬ
ገሀደ ተናገረ ወአየቀ ከመ አልቦ ድኂን እም
እደ ሲኦል በአዝማነ ኦሪት ወነቢያት፡፡ወካዕበ
ይቤ በእንተ ርደተ ነፍሳቲሆሙ ውስተ ሲኦል
እግዚኦ ገደፈከነ ወነሠትከ ቀሠፈከነሂ ወተሣሀ
ልከነ፡፡ዝሰ በእንተ ጸአቶሙ እም ሲኦል በሞ
ተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ አድለቅለቃ ለምድር
ወሆካ፡፡ዝኒ በእንተ አድለቅለቀት ምድር አመ
ፀአተ ነፍሱ እምሥጋሁ፡፡ወፈወስካ ቍስላ
እስመ አንቀልቀለት፡፡ መዝ፹፰፥፵፰

፺፭ ዝኒ በእንተ ክዕወተ ደሙ ለፈውሶ
ቍስሊሃ ወለአጽንዖ መሠረታ ከመ ኢታንቀ
ልቅል፡፡አርአይኮሙ ዕፁባተ ለሕዝብከ፡፡ ዝኒ
በእንተ ጸሊመ ፀሐይ ዘስሱ ሰዓት ወበእንተ
ሥጥቀተ ኰኵሕ ወነቀልቃለ ምድር ወሥ
ጠተ መንጠላዕተ ምኵራብ በጊዜ ተስዓቱ ሰዓ
ት፡፡ወአስተይከነ ወይነ ወደንግጸ፡፡ምንትኬ ው
እቱ ወይን መደንግጽ ዘእንበለ ንቅዐ ደሙ
ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘውሕዘ እምገቦሁ ሶበ
ረገዞ ኰናተ ሐራዊ፡፡አማንኬ ወይን መደን
ግጽ ዘውሕዘ እምገቦ በድን ወአኮ እምገቦ ሕያ
ው፡፡እስመ ሕይወተ መለኮት ህልው ውስቴ
ቱ፡፡ አማንኬ ወይን መደንግጽ ዘንቅዐ እምገቦ
ሁ ለበድን ዘዓርበ ፋሲካ ወአንቅሆሙ ለአብ
ድንተ ትካት እም ንዋመ ሞቶሙ፡፡አማንኬ
ወይን መደንግጽ ዘያደነግፆ ለሰይጣን ከመ
ዘርእየ መብረቀ ዘይነጥር በኃይል ወበአንበል
ብሎቱ ዘያከፍኦ ዓይኖ ለዘይኔጽሮ፡፡

፺፮ ሰትዩ አብድንተ ትካት ዘንቅዓ
እምገቦ በድን ርጡብ ዘዓርበ ፋሲካ፡፡ ወመ
ጠነ ሰዓቱሰ እምጊዜ ሞቱ እስከ ጊዜ ርግዘቱ
ሠለስቱ ሳዕ እስመ በተሰዓቱ ሰዓት ወፅአት
ነፍሱ እምሥጋሁ፡ወበዐሠርቱ ወአሐዱ ሰዓት

የእግዚአብሔር የምሕረቱ ጠል ጠብቃቸዋለችና
ነቢዩ ከአንተ ዘንድ የሚገኝ ጠል ሕይወታቸው
ነው እንዳለ፡፡ አንበሶቹ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ
ሆነው በዳንኤል ላይ ክፉ እንዳላደረጉበት
እንዲሁ የገሃነም ጠባቂዎች በጥልቁ የፍርድ
ቦታ ከእነርሱ ጋር ሳለ በንጹሀን ነቢያት ላይ ክፉ
አላደረጉም፡፡

፺፬ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ
ነቢያት በሲኦል ስለ መኖራቸው ዳዊት በሕይ
ወት በሚኖር ሞትን የማያያት ሰው ማን ነው
ነፍሱንስ ከሲኦል እጅ የሚያድናት ማን ነው
ብሎ ተናገረ በዚህም በኦሪትና በነቢያት ዘመን
ከሲኦል እጅ መዳን እንዳልነበረ በግልጥ ተናገረ
አስታወቀም፡፡ ሁለተኛም ስለነፍሶቻቸው ወደ
ሲኦል መውረድ አቤቱ ጣልኸን አፈረስኸንም
ቀሠፍኸንም ይቅርም አልኸን አለ፡፡ ይህም
በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ከሲኦል ስለ መው
ጣታቸው ነው፡፡ ምድርን አነዋወጥኻት አወ
ክኻትም አለ፡ ይህም ነፍሱ ከሥጋው በምትወጣ
ጊዜ ምድር ስለተናዋወጠች ነው፡፡ መዝ፹፰፥፵፰

፺፭ ተነዋውጣለችና ቁስሏን ፈውስ ህላት
አለ፡ ይህም ቁስሎቿን ለመፈወስ መሠረቷንም
እንይነዋወጥ ለማጽናት ደሙን ስለ ፍሰሱ
የተነገረ ነው፡፡ለወገኖችህ ድንቆችን አሳየህ አለ፡፡
ይህም በስድስት ሰዓት ፀሐይ ስለ ጨለሟ
ስለአለትም መሰነጣጠቅ ስለምድር ንውጽውጽታ
ስለ ምኲራብ መጋረጃ በዘጠኝ ሰዓት መቀደድ
የተናገረው ነው፡፡ ወይን አጠጣኸው አለ
የጭፍራ ጦር በወጋው ጊዜ ከጐኑ ከፈሰሰው
የኢየሱስ ክርስቶስ የደሙ ፈሳሽ በቀር የመ
ንገጥ ወይን ምንድር ነው ከሕያው ጐን ያይደለ
ነፍስ ከተለየው አካልማ የፈሰሰ እርሱ በእውነት
የሚያስደነግጥ ወይን ነው የመለኮት ሕይወ ነት
በእርሱ ውስጥ አለና በዓርብ ምሽት ነፍስ
ከተለየው አካል ጐን የፈሰሰ ቀድሞ ያንቀላትም
በድኖች ከሞታቸው እንቅልፍ ያነቃቸው እርሱ
የሚያስደነገጥ ወይን ነው፡፡በኃይል የሚጮህ ቦግ
ቦግ በማለቱ የሚያየውን ሰው ዓይን የሚያፈ ዝ
መብረቅን እንዳየ ሰይጣንን የሚያስደነግጠው
በእውነት የሚያስደነግጥ ወይን ነው፡፡

፺፮ በፋሲካ ዓርብ ነፍስ ከተለየው
አካል ጐን የፈሰሰውን የጥንት በድኖች ጠጡ
የሰዓቱም ልክ ከሞቱ እስከ መወጋቱ ጊዜ ድረስ
ያለው ሦስት ሰዓት ነው በዘጠኝ ሰዓት ነፍሱ
ከሥጋው ተለየች በአሥራ አንድም ሰዓት ጐኑ

www.ethiopianorthodox.org

ተረግዘ ገቦሁ ወበዐሠርቱ ወክልኤቱ ሰዓት ወደይዎ ውስተ መቃብር፡፡

፶፯ ወበእንተሰ ንብረቶሙ ለነቢያት በናኀይ ውስተ ዓጸደ ደይን እንዘየዐቅቦሙ ጠለ ምሕረቱ ለእግዚአብሔር ዝሙርየ ወልደ እግዚአብሔር ወምእመንየ ስምዐ ቃሉ በከመ ጽሑፍ ውስተ ወንጌለ ሉቃስ: ወሀሎ አሐዱ ብእሲ በዓል ወይለብሰ ሜላተ ወልብሰ ቢሶስ ወቀጠንተ አልባሰ ወይትፌሣሕ ኵሎ አሚረ ወይትፌጋዕ፡፡ ወአሐዱ ነዳይ ዘስሙ አልዓዛር ግዱፍ ውስተ ዴዴሁ ለባዕል ወይሰከብ ወይ ፈቅድ ወይፌቱ ይጽግብ እምፍርፋራት ዘይወ ድቅ እማዕዱ ለባዕል፡፡ወከለባትኒ ይመጽኡ ወይልሕሱ ቍስሊሁ፡፡

፷ ወእምዝ ሞተ ውእቱ ዝኩ ነዳይ ወወሰድዎ መላእክት ውስተ ሕፅኑ ለአብርሃ ም፡፡ወሞተ ውእቱኒ ባዕል ወተቀብረ ወበሲኦ ል አንሥአ አዕይንቲሁ እንዘ ሀሎ ውስተ ሕማመ ደይን፡፡ወርእዮ ለአብርሃም እምርሑቅ ወአልዓዛርኒ ይረፍቅ ውስተ ሕጽኑ፡፡ወጸውዖ ወይቤሎ አባ አብርሃም ተሣሀለኒ ወፈንዎ ለአልዓዛር ከመ ይጥማዕ ጽንፈ አፅባዕቱ ማየ ወያቍርረኒ ልሳንየ እስመ ሐመምኩ በዝ እሳት።ወይቤሎ አብርሃም ተዘከር ወልድየ ዘከመ ፈጋዕከ ወተፈሣሕከ በሕይወትከ ወአል ዓዛርሰ ከማሁ ከመ በተፅናሰ፡፡ወይእዜኒ ከማ ሁ ከመ ይትፌሣሕ ውእቱ በዝየ ወአንተሰ ተሐምም፡፡ወምስለ ዝንቱ ኵሉ ጸድፍ ዐቢይ ይከልአነ ማእከሌነ ወማእከሌክሙ ከመ እለሂ ይፈቅዱ እምለፌ ይኅልፉ ኀቤክሙ ወእለሂ መንገሌክሙ ኢይዕድዉ ኀቤነ፡፡ሉቃ ፲፮÷፲፱-፴፩

፷፩ ሰማዕ ኦ ዕውረ ልብ ዘይቤ እግዚ እነ በወንጌል ወበሲኦል አንሚአ አዕይንቲሁ ወርእዮ ለአልዓዛር ይረፍቅ ውስተ ሕፅኑ ለአብርሃም ኢኮነኬ ውስተ አጸደ ገነት አላ ውስተ አጸደ ደይን፡፡ሶበሰኬ አጸደ ገነት ይእቲ እምኢርእያ ባዕል እስመ ገነትሰ መንገለ ጽባ ሕ ይእቲ ወሲኦልኒ መንገለ ምዕራብ፡፡ ወበእ ንተዝ አዘዙ ሐዋርያት ከመ ይኩን ጸሎቶሙ ለመሀይምናን መንገለ ጽባሕ፡፡አኮ ለምሥራቀ ፀሐይ አላ ለዘያሠርቆ ለፀሐይ፡፡

፷፪ ሶበሰ በእንተ ፀሐይ ተሠርዐ ጸልዮ መንገለ ግጻዌሁ ለፀሐይ በጽባሕ እምኮነ

ተወግቷል በአሥራ ሁለት ሰዓት ወደ መቃብር ጨምረውታልና፡፡

፶፯ ነቢያት የእግዚአብሔር ጠለ ምሕረቱ እየጠበቀቻቸው በሲኦል በዕረፍት ስለ ኖራቸው የቃሉ ምስክርነት በሉቃስ ወን ጌል ውስጥ እንደተጻፈ ምስክሬና መታመኛዬም የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሐር ግምጃና ቀጭን የተልባ እግር የሚለብስ አንድ ባለጠጋ ሰው ነበር ዘወትርም ይደስታል ዕለት ዕለትም ተመ ችቶት በደስታ ይኖራል፡፡ ስሙ አልዓዛር የተባለ አንድ ሰው በባለጠጋው ደጃፍ ወድቆ ይኖር ነበር፡ ከባለጠጋው ማዕድ ከሚወድቀውም ፍር ፋሪ ሊጠግብ ይሻ ይመኝም ነበር፡፡ ውሾችም መጥተው ቁስሎቹን ይልሱለት ነበር፡፡

፷ ከዚህም በኋላ ያ ደሀ ሞተ መላእክ ትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ባለጠ ጋውም ሞቶ ተቀበረ በሲኦል በፍርድ ሥቃይ ውስጥ ሆኖ ዓይኖቹን አቅንቶ አብርሃምን ከሩ ቅ አየው አልዓዛርም በአእቅፉ ተቀምጦ ነበር፡፡ ጠርቶ አብርሃም አባት ሆይ ራራልኝ የጣቶቹ ንም ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን ያቀዘቅዝልኝ ዘንድ አልዓዛርን ላከው በዚህ እሳት ተሠቃ ይቻለሁና፡፡ አለው አብርሃምም ልጄ ሆይ በሕይ ወትህ ዘመንህ ፈጽመህ እንደተደሰትህ አልዓ ዛርም በችግር እንደኖረ አስብ አሁንም እንደ ዚሁ እርሱ በዚህ ፈጽሞ ይደሰታል አንተ ግን ትሠቃያለህ ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ከእናንተም ወደ እኛ ሊያልፉ የሚፈ ልጉ እንዳይሻገሩ ታላቅ ገደል በእኛና በእናንተ መካከል ይከለክለናል አለው፡፡ ሉቃ ፲፮÷፲፱-፴፩

፷፩ አንተ ልብህ የታወረ ጌታችን በወንጌል በሲኦልም ዓይኖቹን አቅንቶ አልዓ ዛርን አብርሃም እቅፍ ተቀምጦ አየው ያለ ውን ስማ በገነት አፀድ እኮ አይደለም በሲኦል ነው እንጂ፡፡ የገነት አፀድ ብትሆን ኖሮ ባለ ጠጋው ባላያት ነበር፡፡ ገነትስ በፀሐይ መውጫ በኩል ናት ሲኦልም በምዕራብ በኩል ናትና ስለዚህም ሐዋርያት የምእመናን ጸሎት ፊትን ወደ ምሥራቅ በማዞር እንዲሆን አዘዙ፡፡ ለፀሐይ መውጫ አይደለም ፀሐይን ለሚያወጣው ነው እንጂ፡፡

፷፪ ወደ ፀሐይ ከበብ ዞሮ መጸለይ ስለ ፀሐይ የተሠራ ሥርዓት ቢሆንስ ኖሮ ጠዋት

www.ethiopianorthodox.org

መንገለ ምሥራቅ ወበምሴትኒ መንገለ ዐረብ በከመ ይገብሩ ፋርስ መምለኪያነ ፀሐይ፡፡ ለነሰ አዘዙነ ከመ ንጸሊ እንዘ ንኔጽር መንገለ ጽባሕ እመሂ ነግሀ ወእመሂ ሰርከ እመሂ በመዓልት ወእመሂ በለያልይ፡፡በእንተ ዘትቤ ቅድስት ኦሪት ወተከለ እግዚአብሔር አምላክ ውስተ ኤዶም ገነተ ቅድመ መንገለ ጽባሕ፡፡ወበእንተዝ አዘዙነ ሐዋርያት ከመ ይኩን ጸሎትነ መንገለ ምሥራቅ፡፡ ዘፍ፪÷፰

፷፫ ንሚጥ ገጸነ እመንገለ ምዕራብ ዘውእቱ መካነ ደይን ማኅደረ ኃጥአን፡፡ ወንትመየጥ መንገለ ጽባሕ ኀበ ሀሎ ገነተ ተድላ ዘውእቱ ማኅደሮሙ ለቅዱሳን፡፡ኀበ ሀሎ መዝገብነ ህየ ሀሎ ልብነ ኀበ ጽጌ ገነት ዘዘዚአሁ ኅበሪሁ ህየ ይኔጽራ አዕይንት አልባቢነ፡፡ኀበ ርኄ አፈው ዘዘዚአሁ መዓዛሁ ህየ ያጼንዋ አእናፊነ፡፡ኀበ አስካለ በረከት ዘበበ፻፻ ሕንባባቲሁ ህየ ያንቀዐድዋ ቀራንብቲነ፡፡ኀበ ዘንሴፎ ንባእ ህየ ንጐድጕድ አንቀጸ፡፡ኀበ ዘንፈቅድ ነጊደ ህየ ናስተዳሉ ስንቀ ጸሎት፡፡ኀበ ዘንትሜነይ ኅዲረ ህየ ናንሶሱ በአእጋረ ኅሊናነ፡፡እስመ በእንተዝ ተሠርዐ ከመ ይኩን ጸሎትነ መንገለ ገነተ ትፍሥሕት እንተ ኀበ ሀገረ እግዚአብሔር፡፡ውእቱሰ እንዘ ሀሎ ይእቲ መንገለ ምሥራቅ ህላዌሃ፡፡

፷፬ ዳንኤልኒ ገብረ አርአያ ዘከመዝ ዐጸወ ኆኅተ ቤቱ ከመ ይጸሊ ወአርኀወ መሳከወ ጽርኁ ዘይኔጽር መንገለ ኢየሩሳሌም እስመ ረሰየ ተስፋ ኅሊናሁ በምድረ ፄዋዌ ፡፡ ወንሕነኒ ይደልወነ ንሚጥ ገጸነ መንገለ ምሥራቅ ሶበ ንጼሊ እንዘ ንሬሲ ተስፋነ መንገለ ገነተ ኤዶም እንተ ተከላ እግዚአብሔር በእንተ አዳም ወአስተዳለዋ ለርስተ ቅዱሳን ፡፡ ዳን ፮÷፲

፷፭ ወበእንተ ሲኦልኒ ከመ መንገለ ዐረብ ይእቲ ይነግር ዳዊት እንዘ ይብል ፍኖተ ግበሩ ለዘዐርገ እንተ ዐርብ እግዚአብሔር ስሙ፡፡ ምንት ውእቱ ዕርገቱ መንገለ ዐረብ ዘእንበለ ፀአቱ እምቀላየ ደይን ዘህላዌሃ መንገለ ምዕራበ ፀሐይ፡፡ወረደ ኀቤሃ በትሕትና ከመ አሐዱ እምኔሆሙ ለፂውዋን ወዐርገ እምኀቤሃ በልዕልና ምስለ ኵሎሙ ነፍሳተ ቅዱሳን፡፡ወበእንተዝ ይቤ ዳዊት ፍኖተ ግበሩ ለዘዐርገ እንተ ዐርብ ሎሙሰ አዕረጎሙ እምቀላየ ደይን ወኢያዕረጎሙ ውስተ ሰማያት አላ

ወደ ምሥራቅ በምሽት ደግሞ ፀሐይን የሚያመልኩ የፋርስ ሰዎች እንደሚያደርጉት ወደ ምዕራብ በሆነ ነበር፡፡ እኛን ግን ጠዋትም ቢሆን ምሽትም ቢሆን በቀንም ቢሆን በሌሊትም ቢሆን ወደ ፀሐይ መውጫ እያየን እንድንጸልይ አዘዙን፡፡ የከበረች ኦሪትም እግዚአብሔር አምላክም በፀሐይ መውጫ በኩል በኤዶም ገነትን ተከለ አለች፡ ስለዚህም ሐዋርያት ጸሎታችን ወደምሥራቅ እንዲሆን አዘዙን፡፡ ዘፍ፪÷፰

፷፫ ፊታችንን የኃጥአን ማደሪያ የሥቃይ ሥፍራ ከሆነ ከምዕራብ እንመልስ፡ የቅዱሳን ማደሪያ ወደሆነ ተድላ ገነት ወዳለበት እንመለስ መዝገባችን ባለበት በዚያ ልባችን ይኖራል፡፧ ኅብሩ የተለያየ የገነት አባባ ወዳለበት የልባችን ዓይኖች ወደዚያ ያያሉ መዓዛው የተለየ ሽቱ ወዳለበት ወደዚያ አፍንጫችን ያሸትታል፡፡ ቅንጣቶቹ በመቶ በመቶ የሆኑ የበረከት ፍሬ ወዳለበት ወደዚያ ሽፋሽፍቶቻችን ያንጋጥጣሉ፡ ልንገባበት ተስፋ ወደምናደርገው ወደዚያ መዝጊያ እናንኳኳ ልንሄድ ወደምንሻው ወደዚያ የጸሎትን ስንቅ እናዘጋጅ ልናደርበት ወደምንመኘው ወደዚያ በኅሊናችን እግሮች እንመላለስ፡፡ ስለዚህ ነገር ጸሎታችን አነዋወሯ በስተምስራቅ ወደሆነች ደስታ ወዳለባት ወደገነት ይሆን ዘንድ ሥርዓት ተሠራ፡፡

፷፬ ዳንኤልም እንደዚህ ያለ አብነት አደረገ ሊጸልይ የቤቱን ደጃፍ ዘጋ ወደ ኢየሩሳሌም የሚያይበትን የቤቱን መስኮት ከፈተ እርሱ በምርኮ ምድር ሆኖ የኅሊናውን ተስፋ ወደ እግዚአብሔር አገር አድርጓልና፡፡ እኛም በምንጸልይበት ጊዜ ተስፋችንን እግዚአብሔር ስለአዳም ወደተ ከላት ለቅዱሳንም ርስት ትሆን ዘንድ ወዳዘጋጃት ወደ ኤዶም ገነት አድርገን ፊታችንን ወደ ምሥራቅ እንመልስ ዘንድ ይገባናል፡፡ዳን ፮÷፲

፷፭ ስለሲኦልም በፀሐይ መግቢያ በኩል እንደሆነች ዳዊት ወደ ፀሐይ መግቢያ ላረገው መንገድ አዘጋጁ ስሙም እግዚአብሔር ነው አለ፡፡ አነዋወሯ በፀሐይ መግቢያ በኩል ከሆነ ከሲኦል ጥልቅ ከመውጣቱ በቀር ወደ ፀሐይ መግቢያ ማረጉ ምንድር ነው፡፡ ከምርኮኞች እንደ አንዱ ሆኖ በትሕትና ወደርሷ ወረደ ከእርሷም ከቅዱሳን ሁሉ ነፍሶች ጋር በልዕልና ዐረገ ስለዚህም ዳዊት ወደ ፀሐይ መግቢያ ላረገው መንገድ አዘጋጁ አለ፡፡ እነርሱን ከሲኦል ጥልቅ አወጣቸው ወደ ሰማያት ግን አላወጣቸውም ደስታ ወደ ሚገኝባት ገነት

www.ethiopianorthodox.org

አብኦሙ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት፡፡ወበከመ ተመሰሎሙ በርደቱ ውስተ ሲኦል ከማሁ ተመሰሎሙ በበአቱ ውስተ ገነት ወከፈለ ርስተ በበሕዘቢሆሙ፡፡ መዝ፳፯፥፬

፳፮ ወበሌሊተ እሑድ ሦጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ እሜጡ በፈቃድየ ብውሕ ሊተ አንሥኣ ወካዕበ ብውሕ ሊተ አንብራ፡፡ ወዘንተ ትእዛዘ ነሣእኩ በኀበ አቡየ፡፡ ወበጽባሕ አስተርአያ ለማርያም መግደላዊት ወሶበ ፈቀደት ተአምኖ ይቤላ ኢትልክፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረጉ ኀበ አቡየ፡፡ ወበዝ አአመርነ ከመ ኢነበረ ሥጋሁ በየማነ አብ እምቅድመ አሚሃ ፡፡ ወእምጊዜ ፱ ሰዓት እስከ ፍና ሰርክ አውጽኦሙ ለነፍሳት በነፍስተ ሥጋሁ ወአኮ በሥጋሁ ወአብኦሙ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት፡፡ እምሴተ ዓርብ እስከ ሌሊተ እሑድ ነበረት ነፍሱ ውስተ ገነተ ተድላ ምስለ ነፍሳተ ጻድቃን እንዘ ትናዝዝ ልሕዋነ ወታስተፌሥሕ ሕዙናነ፡፡ወሥጋሁሰ እምድኅረ ፀአተ ነፍሱ ነበረት ዲበ ዕፀ መስቀል ፫ ሰዓተ እምጊዜ ፱ ሰዐት እስከ ፍና ሰርክ፡፡

፳፯ ወእምሴተ ዓርብ እስከ ሌሊተ እሑድ ነበረት ውስተ ከርሠ መቃብር፡፡ ወበእሑድ ሌሊት አግባኣ ለነፍሱ ውስተ ማኅፈደ ሥጋሁ በከመ ይቤሎሙ ለአይሁድ ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተመቅደስ ወበሠሉስ መዋዕል አነሥኦ፡፡ወውእቱሰ፡፡በእንተ ቤተ ሥጋሁ ይቤሎሙ፡፡ወእምድኅረ ትንሣኤሁሰ ኢረከባ ኃሣር ለትስብእት መለኮት፡ተለዐለት ኀበ ኢትትረከብ ተመሥጠት ኀበ ኢትትለከፍ፡፡ ተንጦልዐ ላቲ መንጦላዕተ እሳት ወተሠወረት በደባትረ ብርሃን፡ ነበረት ዲበ ሰረገላ ኪሩቤል ኀበ ኢይበጽሕ ሕሊና ሰብእ ወኢዘመላእክት አእምሮ፡፡ወበእንተ ትስብእቱ ለወልደ አምላክ ኢተውሳከ አምልኮ ዘናመልኮ በከመ ቀዳሚ ህላዌሁ፡፡ወኢንበል ንሰግድ ለመለኮቱ ወንትቀነይ ለትስብእቱ አላ ንበል ንሰግድ ለመለኮት ዘተሰብአ ወንትቀነይ ለትስብእት ዘተአምለከ፡፡ነአምን ድማሬ እንበለ ቱሳሔ ወጽማሬ እንበለ ሙያጤ፡፡ ዘውእቱ ፩ እግዚአብሔር ወ፩ አካል ወ፩ ራእይ፡፡ ሎቱ ስብሐት እምኀበ ሰብእ ወመላእክት ወእምኀበ ኲሉ ዘፍጡር ወግቡር ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አስገባቸው እንጂ ወደ ሲኦል በመውረዱ እንደ መሰላቸው እንዲሁ ወደ ገነት በመግባቱ መሰላቸው በየወገናቸውም ርስትን አደላቸው፡፡ መዝ፳፯፥፬

፳፮ በእሑድ ሌሊትም ተነሣ ነፍሱን ወደ ሥጋው መለሳት በመለኮቱም ኃይል ተነሣ እርሱ ባለቤቱ ነፍሴን በፈቃዴ እሰጣለሁ አነሣት ዘንድ ሥልጣን አለኝ ዳግመኛም ላኖራት ሥልጣን አለኝ ይህን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ ብሎ እንደተናገረ፡፡ በጠዋትም ለማርያም መግደላዊት ታያት እጅ ልትነሣውም ስትሻ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት፡፡ በዚህም ከዚያን ጊዜ አስቀድሞ ሥጋው በአብ ቀኝ እንዳልተቀመጠ ዐወቅን ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ በአካለ ነፍሱ ነፍሳትን አወጣቸው ደስታ ወዳለበት ገነትም አስገባቸው፡፡ ከዓርብ ምሽት እስከ እሑድ ሌሊት ድረስ ነፍሱ ያለቀሱትን እያጽናናች ያዘኑትንም ደስ እያሰኘች ከጻድቃን ነፍሶች ጋር በተድላ ገነት ቆየች፡፡ ሥጋው ግን ከነፍሱ መውጣት በኋላ ከዘጠኝ ሰዓት እስከ ሠርክ ድረስ ሦስት ሰዓት ያህል በዕፀ መስቀል ላይ ቆየ፡፡

፳፯ ከዓርብ ምሽት እስከ እሑድ ሌሊት ድረስ በመቃብር ውስጥ ቆየ እሑድ ሌሊት ነፍሱን ወደሥጋዋ አዳራሽ መለሳት አይሁድን ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም እሠራዋለሁ እንዳላቸው ይህንንም ስለ ሥጋው ተናገራቸው፡፡ ከትንሣኤው በኋላ የመለኮትን ሰውነት መከራ አላገኛትም ወደ ማትገኝበት ከፍ ከፍ አለች ወደማትነካበትም ተነጠቀች የእሳት መጋረጃ ተጋረደላት በብርሃን ድንኳኖችም ተሠወረች የሰው ኅሊና የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በኪሩቤል ሠረገላ ላይ ተቀመጠች ስለ አምላክ ልጅ ሰውነት እንደቀደመው አነዋወሩ ነው እንጂ የተጨመረ አምልኮ የምናመልከው አይደለም፡፡ ለመለኮቱ እንሰግዳለን ለሰውነቱም እንገዛለን አንበል ሰው ለሆነ ለመለኮቱ እንሰግዳለን አምላክ ለሆነ ለሥጋውም እንገዛለን እንበል እንጂ ያለመቀላቀል መዋሐድን ያለመለወጥም አንድ መሆንን እምናለን፡ ይኸውም አንድ እግዚአብሔር አንድ አካል አንድ መልክ ነው በሰዎችና በመላእክት በፍጥረታትም ሁሉ ዘንድ ለርሱ ምስጋና ይገባል ለዘለላሙ አሜን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፰ ተፈጸመ ዘለፋሆሙ ለአርሲስ ወለመናፍቃን፡ እምጽንዓተ ሰማይ ውዱቃን፡ በአጥባተ ከለባት ልሑቃን፡ ነባብያነ ሐሰት እለ ኢጽዱቃን፡ለአንቀጸ ሲኦል ልጹቃን፡ እለ ይብልዎ ለክርስቶስ በነፍሱ ወሥጋሁ ወረደ ውስተ አዕጻደተ ደይን፡ ይቤ ጊዮርጊስ ወልደ ቅድስት ቤተክርስቲያን፡ስብሐት ለእግዚአብ ሔር ለመኰንነ ሕያዋን ወሙታን፡ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

........... /// ...........

፳፰ ከሰማይ ጠፈር የወደቁ በውሾችም ጡት ያደጉ ከእውነተኞች ያይደሉ ሐሰት ተናጋሪዎች ለሲኦልም ዳር የቀረቡ ክርስቶስን በነፍስና በሥጋው ወደ ሲኦል አፀዶች ወረደ ያሉት አርሲስ የተባሉ መናፍቃን ተግሣጽ ተፈጸመ፡ የቅድስት ቤተክርስቲያን ልጅ ጊዮርጊስ ተናገረው፡ ሕያዋንንና ሙታንን ለሚገዛ ለእግ ዚአብሔር ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን፡፡

........... /// ...........

www.ethiopianorthodox.org